ልማታዊነት ወይንስ ገበያ

በኢትዮ ቴሌኮም

ማቲያስ ገሠሠ

ልማታዊነት ወይንስ ገበያ

በኢትዮ ቴሌኮም

ማቲያስ ገሠሠ

ግንቦት 18, 2018

ማውጫ

1 መግቢያ 1
2 ኢትዮ ቴሌኮም 3
2.1 የሒሳብ አያያዝ ችግር 4
2.2 ቴሌን ለመደገፍ በእሚመስል መንግሥት ከፍተኛ አገልግሎት ከቴሌ ይገዛል 7
2.3 ቴሌ ከፍተኛ የገቢ ዕድገት ቢኖረውም ትርፋማነቱ በእዚያ መጠን አያድግም 11
2.4 የሥራ ማስኬጃ ክፍያ (Operating costs): በእየግዜው ከገቢው በላይ እያደገ ነው 16
2.5 ቴሌ በመስኩ ዝቅተኛ ምርታማነት አለው እሚባል ነው 22
2.6 ቴሌ ከእያንዳንዱ ደንበኛ በአማካኝ ዝቅተኛ ገንዘብ ነው እሚሰበስበው 25
2.7 ቴሌ እሚቀበላቸው ስውር ድጎማዎች 28
2.7.1 ቴሌ እሚጠቀምበትን መሬት አልገዛውም ወይንም ዋጋውን በትክክል አላሰላውም 29
2.7.2 በዓመታዊ ሪፖርቱ ውስጥ የደሞዝ ክፍያው ከተመሳሳይ ተቋማት ጋር አልተነጻጸረም 32
2.7.3 ወደ አክስዮን ገበያ በይፋ መቀላቀል (The IPO) እና ለተከፈለ ክፍያ ምንም ዓይነት ኃብት አለማስተላለፍ 35
2.7.4 የቴሌኮም ገበያ በልማታዊነት በመታገቱ ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ የእሚከፍለው ዋጋ 36
3 ገበያ ምን ማድረግ እንደ እሚችል ያሳየው የሳፋሪኮም መስታወት 37
3.1 የባለቤትነት ጉዳይ 37
3.2 በ2025 የኬንያ መንግሥት የተሻለ ግብር እና የትርፍ ክፍፍል (Dividend) አግኝቷል 38
3.3 ተወዳዳሪ ላልሆነ ተጠቃሚነት የኢትዮጵያ መንግሥት እራሱ ላይ አላስፈላጊ ብዙ ጫና አምጥቷል 39
3.4 የምርታማነት ልዩነት 40
3.5 ሳፋሪኮም በኢትዮጵያ: ተመሳሳይ ገበያ - የተለያየ ሞዴል 41
3.6 ጉዳዩ የባለቤትነት ዓይነት አይደለም ይልቁንም የአስተዳደር ዘዬው ነው 42
4 የልማታዊያኑ መከላከያ — እና የማይሠራበት ምክንያት 44
4.1 ገበያ ገጠሩን የኢትዮጵያ ክፍል አያገለግልም 44
4.2 የቴሌኮም መስክ ከሐገር ደህንነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ነው 46

4.3 የኢትዮጵያ የካፒታል ማርኬት እንደ እዚኽ ዓይነት ሰፊ ፕሮጀክትን ፋይናንስ ሊያደርግ አይችልም 47

4.4 የሲንጋፖር እና የኤምሬት አየር መንገድ በልማታዊ መንገድ ስኬታማ ሆነዋል 48

5 ምክረ ኃሳብ — ከተልዕኮ ወደ ገበያ ሽግግር 50

5.1 አንድ: ቴሌ በአስቸኳይ ገንዘቡን የሰበሰበበትን አክሲዮን ይደልድል (allotment immediately) 54

5.2 ኹለት: መንግሥት በቴሌ ላይ ያለውን ባለቤትነት በ50% ይቀንስ 50

5.3 ሶሥት: ገለልተኛ የሆነ የቴሌኮምንኬሽን መስክን የእሚቆጣጠር ባለስልጣን መሥሪያ ቤት ማቋቋም 51

5.4 አራት: ኹሉም በኢትዮጵያ ገበያ ለመሥራት ፈቃድ የእሚያገኙ የቴሌኮም አገልግሎት አቅራቢዎች መላ ሐገሪቱን በኔትዎርክ ሽፋን ለማዳረስ ስምምነት መፈረም አለባቸው 52

5.5 አምስት: የኢትዮጵያ የቴሌኮም ገበያ ለኹሉም ተወዳዳሪዎች ክፍት መሆን አለበት 52

5.6 ስድስት: ቴሌ ከእዚኽ በኋላ በእሚያወጣቸው ዓመታዊ ሪፖርቶቹ የበለጠ ግልጸኝነት ሊኖራቸው ይገባል 53

1 መግቢያ

ይኸ ልማታዊነት ወይንስ ገበያ በእሚል የእማቀርበው ሦሥተኛ ጽሑፍ ነው።

በመጀመሪያው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኹለተኛው ደግሞ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በልማታዊነት ወይንስ በገበያ ቢመሩ ፤ ለራሳቸውም እንደ ተቋም ፤ በሐገሪቱም ውስጥ እንደ ተቋም ከእሚኖራቸው ሚና አንጻር ፤ የተሻለ ሚና ይጫወታሉ የእሚለውን ለማቅረብ ሞክሬያለኹ።

በእዚኸ በሦሥተኛው ደግሞ ኢትዮ ቴሌኮም ፤ እንደ ተቋም ለራሱም ፤ የኢትዮጵያ ዲጅታይዜሽን መሠረት እንደ ሆነ አንድ ትልቅ ብሔራዊ ተቋምም በኢኮኖሚ ውስጥ ከእሚኖረው ሚና አንጻር ፤ በገበያ ወይንስ በልማታዊነት ቢመራ ይሻላል የእሚለውን ንጽጽራዊ ትንተና ለማቅረብ እሞክራለኹ።

ጠቅለል አድርገን የልማታዊነትን እና የገበያን ልዩነት ከቴሌ አንጻር እናስቀምጥ ካልን ፦

ቴሌ አኹን የእሚመራበት የልማታዊ አሰተሳሰብ ፤ ለመላው ኢትዮጵያ የዘመናዊ ቴሌኮም አገልግሎት የሕዝብን አቅም ባገናዘበ መልኩ የማቅረብ የእሚል ተልዕኮ ለቴሌ ሰጥቶ ፤ እራሱን በቀዳሚነት ይኸን ግብ ከማሳካት እንጂ ከትርፋማነት እና ከምርታማነት አንጻር እንደ አይመዝን በማድረግ ፤ አቋቁሞታል።

ከእዚኽም የተነሳ ቴሌ ፤ ከእዚኽ ተልዕኮው አንጻር ፦ በነሐሴ 2025 ባወጣው ዘገባ መሠረት የ4G ኔትወርክ ሽፋን በሐገሪቱ 70% በማድረስ ፣ የጠቅላላ ደንበኞቹን ቁጥር በ2026 ከ83 ሚልዮን በላይ በማድረግ እና በጠቅላላው የሞባይል ስልክ አገልግሎት በሐገር ደረጃ ተደራሽ በማድረግ ፤ ከፍተኛ እመርታ አስመዝግቧል።

ለአገልግሎት የእሚያስከፍለው ክፍያም ፤ አያዋጣውም ቢያስብለው እንጂ ፤ የሕዝቡን የመግዛት አቅም ከግምት ያስገባ አይደለም የእሚባል አይደለም።

በአንጻሩ የገበያው አስተሳሰብ ደግሞ ፤ ቴሌ በልማታዊነት አስተሳሰብ እየተመራ ይኸ ያስመዘገበው ውጤት እሚናቅ ባይሆንም ፤ ይኸ ግን የተሻለው እና ብቸኛው አማራጭ አይደለም ብሎ ይላል።

ምክንያቱም ፦ ቴሌ ያስመዘገባቸውን ድሎች እንደ ወደር የእማይገኝላቸው ድሎች ብናያቸው እንኳን ፤ እነ እዚኽ ድሎች ፦ ለምሳሌ ፦ ከመንግሥት እና ከሕዝብ በተደረጉ በበርካታ ቢልዮን ብሮች በእሚያወጡ የመሥሪያ ቦታ ድጎማ ፣ በብቸኛ ቀጣሪነት በከፍተኛ ደረጃ የሠራተኛ ደሞዝ ጭቆና ፣ በገበያ ቢሠራ ሊገኙ የእሚችሉ ሌሎች ተቋማዊ እና ሐገራዊ ዕድሎችን በማባከን ፣ ወዘተ የመጡ ናቸው።

በአንጻሩ ግን ቴሌ እንደ ተቋም የሐገሪቱ የቴሌኮምንኬሽን መስክም በጠቅላላው ፤ ቴሌም በተናጠል እንደ ተቋም በገበያ ቢሠሩ ኖሮ ፤ ቴሌ የልማታዊ መንግሥት የሰጠውን ተልዕኮውንም አሳክቶ ፤ መንግሥትን ፣ ሕዝብን እና ሠራተኞቹን ያስከፈላቸውን ዋጋዎች በማስወገድ እንዲያውም መንግሥትን ፣ ሕዝብን እና ሠራተኞቹን ፤ በገንዘብ እና የአገልግሎት ጥራት መመዘኛ በብዙ እጥፍ ይጠቅም ነበር ነው።

ለምሳሌ ፡- በኬንያ የቴሌኮምንኬሽን መስኩ በገበያ እየሠራ ፤ የ4G ሽፋኑን 97% በመቶ በማድረስ እና የእሚያቀርበውንም አገልግሎት ጥራት ከፍ በማድረግ ከቴሌ በእሚሻል መልኩ ከአፍሪካ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያለ ነው።

ስለ እዚኽ ፡- በኬንያ ገበያ ፤ ከተልዕኮም ሆነ ከኢኮኖሚያዊ ትርፋማነት አንጻር ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ችሏል።

በመሆኑም ፡- በእዚኽ በሶስተኛው እና የኢትዮ ቴሌኮምን ፤ ልማታዊነት ወይንስ ገበያ በእሚል በእሚመዝነው ጽሑፍ ፤ ቴሌ ብዙ ድሎች ቢኖሩትም ፤ እነ እዚኽን ድሎች ለማስመዝገበ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፣ መንግሥት እና ሠራተኞቹን ያስከፈላቸውን አላስፈላጊ ዋጋ በማንሳት እና በአንጻሩ ቴሌ በገበያ ቢመራ አኹን ካስመዘገበው ድል በላይ ድል ሊያስመዘግብ የእሚችል መሆኑን እና ያንንም ከፍተኛ ድል በማስመዝገብ ኺደት ውስጥ ፤ አላስፈላጊ ዋጋ ሕዝብን ፣ መንግሥትን እና ሠራተኞቹን ማስከፈል ሳይሆን እንዲያውም ይበልጥ ተጠቃሚ ሊያደርጋቸው እንደ እሚችል በማሳየት ፤ ቴሌ በገበያ ቢመራ ይሻላል ለማለት እሞክራለኹ።

2 ኢትዮ ቴሌኮም

ኢትዮ ቴሌኮም ወይንም በተለምዶ ቴሌ የእምንለው ተቋም ፤ በአጼ ምንሊክ የንግሥና ዘመን ፤ የቴሌግራም ግንኙነትን በሐገር ደረጃ ለማዳረስ ተብሎ በ1886 (በፈረንጆቹ በ1894) ተቋቁሞ ፤ በእየ ግዜው የቴሌኮምንኬሽን አገልግሎት እየዘመነ ሲኼድ እርሱም አብሮ በመዘመን ዛሬ የእሚገኝበት ደረጃ ላይ የደረሰ ነው።

ከተመሠረተበት ግዜ አንስተን ከቆጠርን ፤ ቴሌ የ132 ዓመት የእድሜ ባለጸጋ በመሆኑ ፤ ለምሳሌ ፦ በ1965 ነጻነቷን አግኝታ ሉዓላዊት ሐገር ከሆነችው ኬንያ አንጻር ካየነው ፤ በ71 ዓመት ይበልጣታል።

በእዚኽ መልኩ ከተቋቋመ በኋላ ፤ ምንም እንኳን ፤ ከመንግሥት ንብረትነት የወጣበት ግዜ ባይኖርም ፤ በእየ ግዜው ፤ የመንግሥት አደራረጉ እና አሠራሩ ሲቀየር ፤ በተለያየ መልኩ ሲዋቅር ቆይቷል።

በ2025/2026 84.4 ሚልየን የሞባይል አገልግሎት ተጠቃሚ ደንበኞች እና ወደ 51 ሚልዮን የእሚጠጉ የኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች አንደ አሉት ሪፖርት አድርጓል።

በሰኔ 30, 2025 ዓመታዊ ሪፖርቱ መሠረት ጠቅላላ የሠራተኞቹ ቁጥር 16, 353 እንደ ሆነም ተዘግቧል። በእዚኹ ዓመት ያገኘው ገቢ 148 ቢልዮን ብር ሲሆን ፤ ትርፉም 5.9 ቢልዮን ብር ነበር።

በሐገሪቱ ውስጥ ባለው የማክሮ ኢኮኖሚ አለመረጋጋት ፣ የውጭ ምንዛሪ ችግር እና ቴሌ በእሚመራበት ፍልስፍና ምክንያት ፤ የቴሌን አፈጻጸም በአንድ ዓመት ዓመታዊ ሪፖርት ብቻ ለመረዳት አዳጋች ሆኖ ስለ አገኘኹት ፤ ከ2019 እስከ 2025 ያሉትን የ7 ዓመት ሪፖርት በማየት ቴሌ ፤ በልማታዊ መንገድ በመመራቱ እራሱንም ሐገርንም ያስከፈለውን ዋጋ እና ያሳጣውን ዕድል ለማየት ሞክሬያለኹ።

ከእዚኽ በመቀጠልም ፤ በእነ እዚኽ የሰባት ዓመታት ዓመታዊ ሪፖርቶች ላይ በመደገፍ እና ለንጽጽር የሳፋሪኮምን (ጠቅላላ የኢትዮጵያ እና የኬንያ) የኹለት ዓመት ፤ ማለትም ፦ የ2024 እና የ2025 ዓመታዊ ሪፖርት መሠረት በማድረግ ፤ ዝርዝሩን አቀርባለኹ።

2.1 የሒሳብ አያያዝ ችግር

በሐገራችን የቴሌኮም መስኩን ለግል ገበያ ክፍት መደረግ የለበትም በእሚል ከእሚቀርቡ መከራከሪያዎች አንዱ ፤ መስኩ በጣም ትርፋማ ከመሆኑ የተነሳ ፤ ለገበያ ቢከፈት ነጋዴዎች ብር ማተም እንደ ተፈቀደላቸው ያኽል ከፍተኛ ትርፍ እንዲያገኙ የእሚያደርግ በመሆኑ ፤ ይኽን መሰል ትርፋማ መስክን እንደ ኢትዮጵያ ባለ ድኃ ሐገር ፤ ለግል ከመክፈት በመንግሥት እጅ አቆይቶ ከመስኩ የእሚገኘውን ሰፊ ትርፍ የመንግሥትን በጀት በመደጎም ልማትን ማፋፋም ይገባል የእሚል ነው።

ምንም እንኳን ፤ ይኽ አቋም ትክክል ነው ወይንስ አይደለም የእሚለው እራሱ ፤ በተለይ ከገበያ አንጻር ትክክል አይደለም የእሚለውን አባባል የበለጠ ትክክል ቢያደርገውም፤ አቋሙ ትክክል ሆነም አልሆነም ፤ መጀመሪያ ግን አቋሙ የተመሠረተበት መከራከሪያ (The Premise) ትክክል መሆን አለበት።

እርሱም ፦ የቴሌኮም መስኩ ፤ ትርፋማ ከመሆኑ የተነሳ ፤ ብር “የእሚታተምበት” መስክ መሆን አለበት።

የ7ቱን ዓመት የቴሌን ዓመታዊ ሪፖርት ስንመለከት ፤ ኹለት ይኽን የእሚያፈርሱ ነገሮችን እናገኛለን ፦

1. ቴሌ ከ2021 በፊት ፤ በተለይ ከአንጡራ ኃብት አንጻር (Return on Equity) በጣም ትርፋማ የመሰለው ከመንግሥት በመላ ኢትዮጵያ የወሰደውን ወደ 560 ኼክታር መሬት በዋጋው የሒሳብ መዝገቡ ላይ ባለማስፈሩ ነው ፥
2. አቅምን ያገናዘበ ክፍያ ስለ እሚጠይቅ ነው ትርፋማነቱ ፤ ለምሳሌ ፦ ከሳፋሪኮም አንጻር ዝቅተኛ የሆነው ቢባል ፤ ቴሌ ይኽን “አቅምን ያገናዘበ” ክፍያ የእሚያስከፍለው ከመንግሥት ነጻ የመሥሪያ ቦታ በመውሰድ ስለ እሚደጉም በመሆኑ ፤ ድጓማው ትክክለኛ ድጎማ ሳይሆን የኢትዮጵያ መንግሥት እና ሕዝብ ቴሌን ደጉመው የእሚያገኙት በመሆኑ ፤ የተቋሙን አፈጻጸም ጥያቄ ውስጥ የእሚያስገባ ነው ፥

እነ እዚኽን እንደ መነሻ ይዘን ፤ ስለ ጉዳዩ ትንሽ በዝርዝር ዕንመልከት።

የአንድ ተቋም ትርፋማነት እና አምራችነት ከእሚለካበት መንገድ አንዱ ፤ ተቋሙ ከጠቅላላ ንብረቱ እና ከአንጡራ ኃብቱ (Equity) አንጻር የእሚያተርፈው ትርፉ በእዚያ መስክ ከተሰማሩ ተመሳሳይ ተቋማት ጋር በማነጻጸር ነው።

አንጡራ ኃብት (Equity) የእሚባለው ፤ አንድ ድርጅት ካለው ጠቅላላ ንብረት ላይ ድርጅቱ ያለበት ጠቅላላ ዕዳ ተቀንሶ የእሚቀረው ነው።

እናም ይኽ የተቋማት ትርፋማነት/ምርታማነት የእሚለካባቸው መለኪያዎች ትርፍ በንብረት (ROA – Return on Asset) እና ትርፍ በአንጡራ ኃብት (ROE – Return on Equity) በመባል ይታወቃሉ።

በእዚኽም መሠረት ፤ ቴሌ ከአንጡራ ኃብቱ አንጻር በ2019 እና በ2020 የነበረው ትርፋማነት ምን ያኽል ነበር ብለን ከመዘንን በእሚያስገርም ኹኔታ 82% እና 89% ሆኖ እናገኘዋለን።

እንደ እዚኹም ከጠቅላላ ኃብቱ አንጻር ምን ያኽል አተረፈ (ROA) ካልን ፤ 8% እና 11% አትርፎ እናገኘዋለን ፤ ይኽም ጥሩ የእሚባል የትርፍ መጠን ነው።

	2019	2020
ROA	8.03%	11.98%
ROE	89.05%	82.0%

በእዚኽ መሠረት ካየነው ፤ በእውነትም ቴሌ ፤ በተለይ ከአንጡራ ኃብቱ አንጻር እሚያተርፍ ሳይሆን ገንዘብ የእሚያትም ነው የእሚመስለው ፤ ምክንያቱም በእያንዳንዱ ኢንቨስት ባደረገው ብር የእሚያተርፈው ትርፍ 82 እና 89 ሳንቲም ገደማ በመሆኑ።

ይኽ ኹሉ ግን የቴሌ ከንብረት እና ከአንጡራ ኃብት (Equity) አንጻር ያለ ትርፋማነት ሳይሆን ፤ ከመንግሥት በስጦታ የወሰደውን ወደ 83 ቢልዮን ብር የእሚገመት ወደ 560 ኼክታር መሬት በንብረትነት በአግባቡ ስለ እማይመዘግብ ነው።

አንድ ግዜ ፤ እራሱን ከሳፋሪኮም ጋር ለእሚያደርገው ውድድር ለማዘጋጀት ፤ KPMG የእሚባል የእንግሊዝ የኦዲት ድርጅት በ2023 ቀጥሮ ፤ ኃብቱን ሲያስመረምር ፤ መሬቱ በዋጋው ተሰልቶ የዘንድሮውን ሒሳብ እንደ አያበላሽ ወደ ኋላ ኼዶ 2021 ላይ መመዝገብ አለበት ብሎ ሲል ፤ የቴሌ ንብረት በአንድ ለሌት የ83 ቢልዮን ብር ጭማሪ ስለ አደረገ ፤ በ2021 እና በ2022 ከንብረት አንጻር ትርፋማነቱ ከ11% እና ከ8% ወርዶ 3% እና 4% ሆነ።

ከአንጡራ ኃብት አንጻር የነበረው ትርፋማነት ደግሞ ፤ ከነበረው የ89% እና የ82% በወጣበት አስገራሚ ኹኔታ ወርዶ 5.8% እና 8.8% ሆነ።

	2021	2022
ROA	3.25%	4.76%
ROE	5.86%	8.86%

በሌላ አገላለጽ ፤ ከመንግሥት የወሰደውን ነጻ መሬት እንደ ንብረት ባለ መቆጠሩ ፤ ኢንቨስት ካደረጋት እያንዳንዷ ብር 82 እና 89 ሳንቲም ያተርፍ እና በጣም ትርፋማ ሲመስል የነበረው ቴሌ ፤ ከመንግሥት በነጻ የተሰጠው መሬት በዋጋው ሲሰላ ፤ በተለይ ከአንጡራ ኃብት አንጻር ትርፋማነቱ በብር ከ80 ሳንቲም በላይ ከመሆን በመውረድ በብር 5 እና 8 ሳንቲም ወደ መሆን ደረሰ።

ታዲያ ከአንጡራ ኃብቱ አንጻር በብር 5 እና 8 ሳንቲም የእሚያተርፍ ድርጅት እንዴት አትራፊ ቢቻ ሳይሆን ገንዘብ "አታሚ" ሊባል ይችላል?

ይኸ የሆነው ፤ ቴሌ ተጠያቂነት ስለ አልነበረበት እና ሒሳቡን በአግባቡ እንዲይዝ የእሚያስገድደው ኹኔታ ስለ ነበረበት ብቻ እንጂ እጅግ አትራፊ ስለ ሆነ አልነበረም።

ከእዚም ጋር አብሮ የቴሌኮም መስኩ በጣም አትራፊ በመሆኑ ፤ ለግል መስክ ክፍት መሆን የለበትም የእሚለው መከራከሪያም አብሮ ይጠፋል። ምክንያቱም ፦ አይደለም ወረድ ብለን በእምናያቸው ምክንያቶች በእዚኸ መልኩ በጣም ዝቅተኛ አትራፊ የሆነው ቴሌ ፤ በመስኩ ተወዳዳሪ የእሚባሉት የእሚያተርፉት ትርፍ በሌላው በማንኛውም መስክ ከእሚገኘው ትርፍ ብዙም የተለየ ሆኖ አናገኘውም።

ስለ እዚኸ ፦ የቴሌኮም መስኩ ትርፋማነት ፤ በኮንስታራክሽን ፣ በባንኪንግ ፣ ወዘተ መስኮች ከእሚገኘው ትርፍም ይኸ ነው የእሚባል ልዩነት የሌለው በመሆኑ ፤ ቴሌ ገንዝበ የእሚታለብበት ላም ነው እና ለግል መሸጥ የለበትም የእሚለው መከራከሪያ ትክክል አይደለም።

በስተመጨረሻም ፤ ቴሌ በኢትዮጵያ ውስጥ የእሚያቀርበው አገልግሎት ፤ ከክፍያ አንጻር ምንም በእማያጠራጥር መንገድ ፤ በአፍሪካ በጣም ዝቅተኛ የእሚባለው ዋጋ ነው። ሆኖም ይኼ የዋጋ ቅናሽ ከቴሌ ተወዳዳሪነት የመጣ ሳይሆን ፦ ከመንግሥት ፣ ከሠራተኞቹ እና ከሕዝብ በመጣ በርካታ ስውር ድጎማ ነው።

ከእዚያኸም በላይ ግን ፤ ልማታዊነት በኢትዮጵያ የሰውን የመግዛት አቅም በማሳደግ ሳይሆን የዜጋው ድህነት የዛሬ 40 ዓመት የእሚፈታ ዓይነት የሩቅ ተስፋ አድርጎ እስከ እዚያአገልግሎት ለማርከስ የእሚፈልግ በመሆኑ እና ይኸም አካኼድ በአንድ በቴሌ ብቻ ሳይሆን ወረድ ብለን እንደ እምናየው ፤ የኬንያ ሕዝብ እንኳን ከኢትዮጵያ ሕዝብ አንጻር የመግዛት አቅሙ በጣም ከፍተኛ እንዲሆን አድርጎ ፤ መንግሥት ተበድሮ እና ተለክቶ ብሎም ስውር ዋጋዎችን ራሱን እና የኢትዮጵያን ሕዝብ አስከፍሎ ዘመናዊ አገልግሎት ቢያቀርብም ፤ ዜጋው ግን ኪሱ ስለ አልጠና ፤ ለምሳሌ ፦ ከኬንያ ሕዝብ እንኳን ስድስት እጥፍ ያነሰ አገልግሎት ነው በዓመት የእሚገዛው።

በአጭሩ የኢትዮጵያ መንግሥት ድህነትን ዜጋውን በማበልጸግ ሳይሆን በስውር ዋጋ ክፍያን በመቀነስ ለመዋጋት ስለ ፈለገ ፤ በሐገር ደረጃ መዋቅራዊ ለውጥ በማድረግ ኢትዮጵያን ኢንደስትራላይዝ የእሚያደርግ ዕድገት ማስመዝገብ አልተቻለም።

2.2 ቴሌን ለመደገፍ በሚመስል መንግሥት ከፍተኛ አገልግሎት ከቴሌ ይገዛል

የኢትዮጵያ መንግሥት ከሚያስፈልገው እና ሊጠቀምበት ከሚችለው በላይ እና ቴሌን ለመደገፍ በሚመስል መንገድ አገልግሎት ከቴሌ የሚገዛ ከሆነ ፤ ቴሌ ከመንግሥት የሚያገኘው ድጎማ ፤ የመሬት እና መሰል ድጎማዎች በማግኘት ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ፤ የአላስፈላጊ ወይንም ከሚፈለገው በላይ በሚደረጉ እና ያው ከሕዝብ ከሚሰበሰብ ግብር ወይንም በሕዝብ ስም ከሚወሰድ ብድር የሚከፈል አገልግሎትም ነው ማለት ነው።

ለምሳሌ ፦ የ2025 የቴሌን ዓመታዊ ገቢ ካየን ፤ በ2024 ከነበረበት 91 ቢልዮን የ62% ዕድገት በማሳየት 148 ቢልዮን ደርሶ እናየዋለን።

ይኽን የቴሌን የ62% ዓመታዊ ገቢ ዕድገት በዝርዝር ስናይ ፤ የልማታዊውን መንግሥት ፍልስፍና ያለበትን መዋቅራዊ የታማኝነት ችግር የሚያጋልጥ ነገር እናገኛለን።

ምክንያቱም ፦ የ2025 የቴሌን ገቢ በዝርዝር ስንመለከት ፤ የዓመታዊ ገቢው በተጋነነ መልኩ በ62% እንዲጋሽብ ካደረጉት ነገሮች መካከል ፤ ከፍተኛ የሆነ ለመንግሥት የተሸጠ የሚመስል የአገግሎት ክፍያ እናያለን።

ኢንተርፕራይዝ ሶሊሽንስ (Enterprise Solution) የሚባለው አገልግሎት በ2025 በአንድ ዓመት ብቻ ገቢው ከ2 ቢልዮን ብር ወደ 9.4 ቢልዮን በመድረስ የ360% ዕድገት አሳይቷል።

በመላው ምድረ አፍሪካ ብናስስ በ12 ወራት ብቻ ፤ የግሉ ዘርፍ የአይቲ (IT) ፍላጎት በ360% አድጎ አናገኝም ፤ በእዚኽ መልኩ የኢትዮጵያን የግል ዘርፍ ከሌሎቹ የአፍሪካ ጓደኞቹ የሚለየው ምንም ምክንያት ስለ እማይኖር ይኽን ያኽል የኢንተርፕራይዝ ሶሊሽንስ ግዢ ከግሉ ዘርፍ ነው የመጣው ልንል አንችልም።

ስለ እዚኽ፦ ይኽ የኢንተርፕራዝ ሶሊሽን የተባለው አገልግሎት በገፍ የገዙት ፦ የመንግሥት የምኒስትር መሥሪያቤቶች ፣ የክልል መንግሥታት ፣ የመንግሥት ባንኮች ፣ የመንግሥት ዩኒቨርስቲዎች ፣ ሆስፒታሎች እና የመንግሥት የደህንነት ተቋሞች ናቸው የሚሆኑት።

ይኽም ሊሆን የሚችለው ፤ መንግሥት በፖሊሲ ደረጃ በትዕዛዝ እነ እዚኽን አገልግሎቶች ፤ በቀጥታም ይኹን በተዘዋዋሪ ፤ ከኢትዮ ቴሌኮም ግዙ ብሎ ከማለቱ የሚመጣ ነው የሚሆነው።

ይኽ ግን የቴሌን የገበያ ትርፋማነት አያሳይም። ይልቁንም መንግሥት ያችኑ የልማታዊነት አካኼዱን ውጤታማነት ለማሳየት ፤ ከሕዝብ የሚሰበስበውን ግብር እና በሕዝብ ስም ለምኖ የሚያመጣውን የእርዳታ ገንዘብ ፤ ከእራሱ ለእራሱ እየሸጠ ፤ ቴሌን እኔ በማስተዳደሬ ገቢውን አሳድጌያለኹ ሊልበት ነው።

ሌላው የፋይዳ መታወቂያ ገቢ ነው። በ2024 የፋይዳ መታወቂያ አልነበረም።

በ2025 ቴሌ ከፋይዳ አገልግሎት የሰበሰበው ገቢ 2.94 ቢልዮን ወይንም 3 ቢልዮን ብር ገደማ ነው። ይኽ ገቢ ቴሌ በ2025 አስመዘገብኹት ካለው የተጣራ ትርፍ ግማሹ ነው። ዓመታዊ ሪፖርቱ በግልጽ ፤ ከፋይዳ ምዝገባ እና መታወቂያ ህትመት ቴሌ 3 ቢልዮን (2.94) ብር ሰበሰበ ብሎ ያስቀምጣል።

እንደ እኔ ግምት ፤ መታወቂያውን ሌላ ቦታ ማሳተም በፍጹም አይቻልም ብሎ ሲደባደብ የነበረውም ፤ በእዚኽ መልኩ ከመታወቂያ ሕትመት ከሕዝቡ ገንዘብ ለመሰብሰብ ይሆናል እንጂ ፤ በገበያ ዋጋ ቢሰላ ፤ የመታወቂያው ሕትመት ያን ያኽል አይጠይቅም ይሆናል።

ይኽ ነው የልማታዊነት ትሩፋት ፤ ሕዝብ የእማይነገረውን ዋጋ እንዲከፍል ማድረግ። ይኽ መንግሥታዊ ማጭበርበር እና ዘረፋ ካልሆነ ምን ሊሆን ይችላል?

ያም ብቻ ሳይሆን ፤ ለመንግሥት በትዕዛዝ የተሸጡ አገልግሎቶች እና በፋይዳ ምክንያት የተገኘው ይኽ ወደ 3 ቢልዮን የእሚጠጋ ገቢ ፤ የቴሌን የአፈጻጸም ብቃት እና ተወዳዳሪነት በፍጹም አያሳይም ፤ ይልቁንም የልማታዊ መንግሥት የሕዝብ አጋችነት እና ሕዝብን ዋጋ አስከፋይነት ነው የእሚያሳየው።

ችግሩ መንግሥት እንዲኽ ለምን ታደርጋለኽ ሲባል ፤ አቅምን ለማገናዘብ ርካሽ አገልግሎት ለማቅረብ ነው ብሎ ይመልሳል። ዕውነታው ግን ዋጋ ሳይከፈል የእሚገኝ አገልግሎት ባለመኖሩ ፤ ሕዝቡ ያልተነገረው ብዙ ዋጋ እየከፈለ ነው ፤ ርካሽ የቴሌ አገልግሎት የእሚያገኘው።

እንደ እዚኹም የክላውድ አገልግሎት (Cloud Service) ምንም እንኳን መጠኑ ትንሽ ቢሆንም የ162% ዕድገት አሳይቷል። ይኽንም በኢትዮጵያ ውስጥ ካለው የትንንሽ እና መካከለኛ የንግድ ድርጅቶች (SMEs) የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እና የክላውድ አጠቃቀም ተነስተን ፤ በአንድ ዓመት የ162% በመቶ ዕድገት እንደ እማያሳዩ መገመት እንችላለን። ሰለ እዚኽ ፦ በእዚኽ ዘርፍም የተመዘገበው ዕድገት በዋናነት ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች የመጣ ነው ማለት እንችላለን።

በመሆኑም ፤ በእዚኽ በክላውድ ሰርቪስ አገልግሎቱም ፤ የቴሌ የገበያ ተወዳዳሪነት እና አምራችነት ዕድገት ሳይሆን ፤ ከመንግሥት የግራ ኪስ ወደ መንግሥት የቀኝ ኪስ የተዘዋዋረ እና ያንኑ ደካማ የልማታዊነት ስኬታማነት ለማሳየት የእሚቀርብ የይስሙላ የገቢ ዕድገት ነው።

በነገራችን ላይ ፤ በእዚኽ መልኩ የመንግሥት ተቋማት በትዕዛዝ የቴሌን አገልግሎት እንዲገዙ ስለ ተደረጉም ይመስላል ፤ በእዚኹ በ2025 ቴሌ ፤ አገልግሎት ሰጥቼ ክፍያ በመከልከል የከሠርኩት ክስረት መጠን 2.2 ቢልዮን ብር ሆኗል ብሎ ሪፖርት ያደረገው እንጂ ዜጋ አገልግሎት ተቀብሎ ክፍያ አልከፍልም ቢል ፤ ካለው ልምድ ፤ መንግሥት እሚለቀው አይመስልም።

በጠቅላላው ፤ ተገቢው ጥንቃቄ ተደርጎ ፤ ቴሌ ፦ በ2025 ከኢንተርፕራይዝ ሶሊሽንስ ፣ ከክላውድ ፣ ከፋይዳ መታወቂያ እና ከመገልገያ መሣሪያዎች ሽያጭ ያገኘውን ተጨማሪ ገቢ ስንደማምር ፤ ጭማሪው በጠቅላላ ወደ 14.4 ቢልዮን ብር ይመጣል ፤ ከጠቅላላው የገቢ ጭማሪ አንጻር የ25% ጭማሪ ለመንግሥት የተሸጠ አገልግሎት ካሳየው ጭማሪ ሆኖ።

ይኸም ገቢ ከቴሌ ተወዳዳሪነት እና አምራችነት የመጣ ሳይሆን ቀጥተኛ በሆነ የመንግሥት ትዕዛዝ ለቴሌ የተፈጠረለት የገቢ ምንጭ ነው።

ይኸን ከመንግሥት ትዕዛዝ የመነጨ 14.4 ቢልዮን ብር ገቢ ፤ ቴሌ በዶላር ክፍያቸውን ከእሚቀበለው :-

- ኢንተርኮኔክት (Interconnect) ፥
- ሊዝድ ሠርኪውት (Leased Circuit) እና ፥
- ሮሚንግ (Roaming)

ከእሚባሉት አገልግሎቶች ፤ የብር የዶላር ምንዛሪ በመቀነሱ ብቻ ካገኘው የንፋስ አመጣሽ (ያለ ምንም ተጨማሪ ምርታማነት በምንዛሪ ማስተካከያ ብቻ የተገኘ የትርጉም ትርፍ (Translation Gain)) 15.7 ቢልዮን ብር ገቢ ጋር ስንደምረው ፤ እንደ እዚኹም :- በእዚያው ዓመት የሰብስክሪፕሽን እና የኢንተርኔት ዋጋ ፤ አንዳንዶቹን ከግማሽ በላይ ከመጨመሩ ጋር ሲደማመር እና ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ ከእዚኽ የዋጋ ጭማሪ ጋር ተያይዞ የመጣ በትንሹ ወደ 3 ቢልዮን ብር ሲጨመርበት ፤ ወደ 32 ቢልዮን ብር የእሚሆነው የዋጋ ጭማሪ የመጣው :-

- መንግሥት ብዙ አገልግሎት በመግዛቱ ፥
- ቀላል የእማይባል የዋጋ ማስተካከያ በመደረጉ ፥
- እና ንፋስ አመጣሽ የእሚባለው የምንዛሪ ለውጥ ፤

ያመጣው ይሆናል።

ያም ማለት :- ጤናማ የሆነው ከተገልጋይ እና ከአገልግሎት ጭማሪ :- ከዳታ ፣ ከድምጽ ፣ ከቴሌብር ፣ ከአዲስ ደንበኞች የመጣው የገቢ ዕድገት ከ56.6 ቢልዮን ብር ወደ 24 ቢልዮን ብር ዝቅ ይላል።

ይኸም ማለት የቴሌ የ2025 የገቢ ዕድገት 26% እንጂ 62% አይደለም የእሚለውን ያስከትላል።

በእርግጥ የ26% ዕድገት ራሱ በጣም ትልቅ እና እሚያስመሰግን ዕድገት ነው ፤ ቀደም ብለን እንደ አልነው ግን ፤ የ62% ዕድገት ግን አይደለም።

ሚዛናዊ ለመሆን :- የቴሌ ዓመታዊ ሪፖርት የኢንተርፕራይዝ ሶሊሽኖቹን እና የክላውድ አገልግሎቶችን ተጠቃሚዎች ፤ ቢያንስ ለምሳሌ :- መንግሥት እና የግል ተቋማት ብሎ ዘርዝሮ ስለ እማያስቀምጥ ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ካለው ተጨባጭ ኹኔታ ተነስቶ ፤ እነ እዚኽን አገልግሎቶች በእዚኽ መጠን በአንድ ዓመት ውስጥ የእሚገዛ የግል የንግድ ተቋም የለም ከእሚል ፤ የተማረ ግምት ላይ ተመስርተን እንጂ ፤ ዓመታዊ ሪፖርቱ የግል እና የመንግሥት ብሎ ከፋፍሎ ስለ እሚያቀርባቸው አይደለም። የብሔራዊ መታወቂያው ግን ፤ በግልጽ የእሚታወቅ ስለ ሆነ ፤ ምንም አያጠራጥርም።

በቴሌ ዓመታዊ ሪፖርት መሠረት ፤ የተጠቀሱት አገልግሎቶች ዓመታዊ ገቢ እና ዕድገታቸው በብር ሲገለጽ :-

	2025	2024	ዕድገት በፐርሰንት
የክላውድ አገልግሎት	268,003,000	102,209,000	162%
የኢንተርፕራይዝ ሶሊሽንስ	9,400,759,000	2,040,394,000	360%
የመገለገያ መሣሪያዎች ሽያጭ	9,153,386,000	5,188,270,000	76%
የፋይዳ መታወቂያ	2,940,749,000	0.00	አዲስ
ድምር	21,762,897,000	7,330,873,000	196%

2.3 ቴሌ ከፍተኛ የገቢ ዕድገት ቢኖረውም ትርፋማነቱ በእዚያ መጠን አያድግም

አንድ የንግድ ተቋም ፤ በከፍተኛ ደረጃ ገቢውን እያሳደገ ፤ ገቢው በእሚያድግበት ፍጥነት እና አግባብ ትርፋማነቱ እማያድግ ከሆነ ፤ ያ ኩባንያ ትርፋማ እና አምራች ኩባንያው ነው ማለት አይቻልም ምክንያቱም ፤ ገቢውን ወደ ትርፍ መቀየር እማይችለው የአሠራር ወይንም የአፈጻጸም ችግር ስለ አለበት ነው።

እስከ 2025 በነበሩት 7 ዓመታት የቴሌ ትርፍ አካኼድ የእሚከተለውን ይመስላል ፡-

ዓመት	ገቢ	ትርፍ	ትርፍ ከገቢ አንጻር
2019	36,405,691,000.00	6.3 ቢልዮን	17.40%
2020	47,628,412,000.00	9.5 ቢልዮን	19.85%
2021	55,499,196,000.00	5.6 ቢልዮን	10.06%
2022	59,448,361,000.00	9.0 ቢልዮን	15.14%
2023	71,525,993,000.00	18.0 ቢልዮን	25.20%
2024	91,371,290,000.00	19.0 ቢልዮን	20.81%
2025	148,050,402,000.00	5.8 ቢልዮን	3.91%

በእነ እዚኽ ሰባት ዓመታት የቴሌ ገቢ በ2019 ከነበረበት 36.4 ቢልዮን አንስቶ በ2025 148.1 ቢልዮን ገደማ በመድረሱ ዕድገቱ የ307% ነው።

ሆኖም የቴሌ የ2019 ትርፍ ከ2025 ትርፍ ጋር ከተነጻጸረ ፤ የቴሌ ዓመታዊ ትርፍ ከ6.3 ቢልዮን ወደ ወደ5.8 በመቀነስ የ8% ቅናሽ አሳይቷል።

በሌላ መንገድ እንመልከተው ካልን ደግሞ ፤ በ2025 የ148 ቢልዮን ብር የእሚያኽል ከፍተኛ መጠን ያለው ገቢ የሰበሰበ አንድ ኩባንያ ያተረፈው ትርፍ ግን 5.8 ቢልዮን ብር ብቻ ነው ማለት ነው ፤ ይኽም ማለት ከገቢው አንጻር የቴሌ ትርፋማነት 3.9% ነው ማለት ነው።

ለንጽጽር እንዲያግዛችኹ ፤ ይኽን አስቡ ፡- አብዛኛው የኢትዮጵያ ባንኮች በቁጠባ ሒሳብ ላይ ከ5% በላይ ወለድ ስለ እሚከፍሉ ፤ መንግሥት ይኽን ግቢ ባንክ ሒሳብ ከፍቶ ቢቆጥበው ፤ የተሻለ ትርፍ ያገኝበት ነበር ።

የ331 ቢልዮን ብር ንብረት ይዞ እና በዓመት የ148 ቢልዮን ብር ገቢ እያመነጨ ፤ አንድ ኩባንያ በዓመት የእሚያተርፈው ትርፍ 5.8 ቢልዮን ብር ብቻ ከሆነ ፤ ይኽ ኩባንያ እያመረተ እና እየተወዳደረ ሳይሆን ፤ ከፍተኛ መጠን ያለው ኃብት ዝቅተኛ ትርፋማነት ባለው መስክ ላይ እያዋለ ፤ ብዙ አዳዲስ እና የበለጡ ኃብት መፍጠሪያ ዕድሎችን እያባከነ ነው።

በ2021 ምንም እንኳን ገቢው ከ47.6 ቢልዮን ብር ወደ 55.5 ቢልየን በማደግ የ15% ዕድገት ቢያሳይም ፤ በእዚያው ዓመት ትርፉ ግን የ40% ገደማ ቅናሽ በማሳየት ከ9.4 ቢልዮን ብር ወደ 5.5 ዝቅ ብሏል።

ይኽ ግን በአጋጣሚ የሆነ ሳይሆን ፤ እንደ እሚመስለው ፤ ቴሌ የቀጥታ እና የሥራ ማስኬጃ ወጪውን ቢያንስ በ2021 ከ6 ቢልዮን ብር በላይ በማሳደጉ ፤ ገቢው ቢጨምርም ትርፉን ግማሽ ሊባል በእሚችል ደረጃ በ40% ገደማ ስለ ቀነሰበት ነው(ምን አልባት ያ ግዜ ሳፋሪኮም ወደ ኢትዮጵያ ገበያ ሊገባ ስለ ነበር ፤ ቴሌ በአፈጻጸም ብቃት መወዳደር ስለ እማያውቅበት)።

በ2023 ከ2022 አንጻር ትርፋማነቱ በእጥፍ ያደገ እና ይኽም ትርፋማነት በ2024 የቀጠለ ይመስላል። ሆኖም የእዚያን ወቅት የቴሌ አመታዊ የገቢ ዘገባ (Income Statement) ሲታይ ፤ ይኽ ትርፋማነት ከቴሌ የአገልግሎት ሽፋን መጨመር እና የአገልግሎት አሰጣጥ ብቃት መጨመር የመጣ ሳይሆን ፤ ይልቁንም ከቴሌ ተወዳዳሪነት መሻሻል ጋር ብዙም ግንኙነት ከሌላቸው ነገሮች የመጣ ሆኖ ፤ ቴሌ ስር የሰደደ መዋቅራዊ ችግር እንደ አለበት የእሚያሳዩ ናቸው።

ለምሳሌ ፦ በ2023 እና በ2024 ትርፉ በእዚኽ መልኩ በከፍተኛ ደረጃ ለማደጉ ሊጠቀሱ የእሚችሉ ኹለት ዋነኛ ምክንያቶች አሉ ፦

- አንዱ ሌሎች ገቢዎች (Other Incomes) የእሚባለው እና ለምሳሌ ፦ ቴሌ ካዝና ውስጥ ዶላር ኖሮ የዶላር ዋጋ ቢጨምር የእሚያገኘው ጭማሪ ፣ አሮጌ መኪና እና ብረታ ብረት ወዘተ ሲሸጥ የእሚያገኛቸው ወይንም በአጠቃላይ የቴሌኮም አገልግሎት በመስጠት ሳይሆን ከመደኛ የቴሌኮም አገልግሎቶች ውጭ ባሉ እነ እዚኽን በመሳሰሉት መንገዶች የእሚያገኛቸው ገቢዎች ፤ በ2023 ከ2022 አንጻር የ135.8 ዕድገት በማሳየት ከ2.1 ቢልዮን ብር ወደ 5.5 ቢልዮን ብር ዕድገት አሳይተዋል። ስለ እዚኽ በእዚያ ዓመት ቴሌ ፤ ለምሳሌ ፦ አሮጌ ዕቃ በመሸጥ እና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወደ 3.4 ቢልየን ብር ተጨማሪ ገቢ አግኝቷል።
- እንደ እዚኹም በእዚያው በ2023 ከ2022 አንጻር ለተበደረው ብድር የእሚከፍለው ክፍያ ከ7 ቢልዮን ብር ወደ 2.9 ቢልዮን ብር ቀንሷል ፤ ይኽም ወደ 4 ቢልዮን የእሚጠጋ ብር ከወጪው ላይ ይቀንስለታል። ይኽም የሆነበት ምክንያት ፤ እንደ እሚመስለው ፤ በ2023 በጠቅላላ ከነበረበት የ3 ቢልዮን ዶላር ብድር ፤ አንዱን ከZTE በ1.5 ቢልዮን ዶላር የተበደረውን ብድር ክፍሎ በመጨረሱ ፤ ከእዚያ ጋር በተያያዘ ይከፍለው የነበረው የወለድ እና ወለዱን የእሚያንረው የውጭ ምንዛሪ ለወጥ በመቀነሱ ነው።

እነ እዚኽ ኹለቱ ተደማምረው ፤ በጠቅላላው ወደ 7.15 ቢልዮን ብር ጭማሪ ስለ ሰጡት የ2023 ትርፉ በእዚኽ መንገድ በእጥፍ ያደገው።

ይኽን ከአፈጻጸም መሻሻል እና ከአገልግሎት አቅርቦት ዕድገት ያልመጣ ወደ 7.15 ቢልዮን ብር ስንቀንስ የ2023 የቴሌ ትርፍ ወደ 11 ቢልዮን ብር ገደማ በመውረድ ፤ ከባለፈው ዓመት አንጻር ጤናማ ዕድገት ወደ እሚመስለው በታው ይመለሳል።

በ2023 የቴሌ ትርፋማነት ከአፈጻጸም ብቃቱ መሻሻል እንደ አልመጣ ፤ በእዚያ ዓመት የነበረውን የገቢ እና የስራ ማስኬጃ ወጪውን (Operating Expense) መመልከት ፤ ጥሩ መረጃ ይሰጣል።

በእዚያው ዓመት ገቢው 20.3% በመቶ ሲያድግ የሥራ ማስኬጃ ወጪው (Operating Expense) ግን በ32.7% ነበር ያደገው።

አንድ ተቋም ደግሞ ዋንኛው ገቢው ከእሚጨምርበት ፍጥነት በላይ የሥራ ማስኬጃ ወጪው የእሚጨምር ከሆነ ፤ ያ ኩባንያ የሥራ ማስኬጃ ወጪውን ገቢውን እና ትርፋማነቱን በእሚያሳድግለት መንገድ እያወጣ አይደለም ማለት ነው።

የ2024 ታሪኩም ተመሳሳይ ይዘት ያለው እና የቴሌን ትልቅ መዋቅራዊ ችግር የእሚያሳይ ነው።

ምንም እንኳን ገቢው በ2023 ከነበረበት 71.5 ቢልዮን ብር ወደ 91.3 ቢልዮን ብር በማደግ የ28% ጭማሪ ቢያሳይም ፤ በእዚያው ዓመት ቀጥታ ወጪ (Direct Costs) ለእሚባሉት እና ለምሳሌ ፦ የውጭ ሐገር ኔትዎርክ ለመጠቀም የእሚከፈሉ ክፍያዎች (በ41% አድጓል)፣ የኔትውርክ ጥገና እና እገዛ አገልግሎት ክፍያም (በ32% አድጓል) ፣ የእጅ ቀፎ እና ሌሎች መሣሪያዎች ግዢም በ36% በመቶ አድጓል ፣ እንደ እዚኹም የኮሚሽን ክፍያ በ35% ሲያድግ ፤ የማቴሪያል ግዢ በ40% ፤ በጠቅላላው የቀጥታ ክፍያ (Direct Cost) የ36% በመቶ ጭማሪ አሳይቷል።

በተመሳሳይ የሥራ ማስኬጃ (The Operating Expense) እንደ እዚያው በጠቅላላው ወደ 40.8% አከባቢ አድጓል።

ይኽም የእሚያሳየን ፤ ቴሌ በ2024 ገቢው ከ71.5 ወደ 91.3 በማደግ የ28% ዕድገት ቢያሳይም ፤ በእዚያው ዓመት ለቀጥታ እና ለሥራ ማስኬጃ ክፍያዎች ያወጣው ወጪ በጠቅላላው በአማካይ በ38.9% ገደማ ስለ አደገ ፤ ቴሌ ገቢው ከእሚያድግበት በላይ ወጪውን እያሳደገ ፤ ተወዳዳሪነቱን እና አትራፊነቱን እየጎዳ እንደ ሆነ ነው።

ከእዚኽም የተነሳ ፤ ምንም እንኳን ገቢው በ20 ቢልዮን ብር ቢያድግም ፤ የ2024 ዓመት ትርፉ ከ2023 አንጻር የጨመረው በ985 ሚልዮን ወይንም ወደ 1 ቢልዮን ገደማ ብቻ ነው ፤ ምክንያቱም ፦ አብዛኛውን ገቢውን ፤ ከገቢው አንጻር ከፍተኛ የነበሩት የቀጥታ እና የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች ስለ ወሰዱት።

የ2024 ትርፉ እንደ 2023 ትርፉ ከፍ ብሎ ብሎ በመቆየት 19 ቢልዮን መሆን የቻለውም ፤ እንደ 2023 ኹሉ ሌላ ገቢ (Other Incomes) ከእሚባሉት ገቢዎች 4.294 ቢልዮን ብር ገቢ ስለ አገኘ እና የእዚያው

ዓመት የዕዳ ክፍያው ፤ አንዱ ትልቁ የZTE በድር ቀደም ብለን እንደ አልነው ተጠናቆ ተከፍሎ ስልነበር ከ2023 የዕዳ ክፍያ ይኸ ነው የእሚባል ልዩነት ሳይኖረው ፤ በመቀጠል ፤ የወለድ እና ወለዱን የእሚያንረው የብር ምንዛሪ መዳከም የእሚያስከትለው ወጪ 3 ቢልየን ብቻ በመሆኑ ነው።

ለእዚያም ነው ፤ በ2025 በውጭ ምንዛሪ መዳከም ምክንያት ቴሌ የከፈለው የወለድ መጠን በአንድ ግዜ ከ3 ቢልዮን ወደ 42 ቢልዮን ብር ያደገው እና የ2025 ትርፉን በ2024 ከነበረበት 19 ቢልዮን ወደ 5.9 ቢልዮን ያወረደው አንዱ ትልቁ ምክንያት የሆነው።

ምን አልባት የውጭ ምንዛሪው እንደ እሚደረግ ቴሌ ስለ አላወቀ ወይንም ቢያውቅም እንኳን ብሩ ቢገኝም ዶላሩን ማግኘት አይቻልም ሊባል ይችላል እንጂ ፤ ለትንታኔ ያክል ቴሌ ፦

- ምንዛሪ እንደ እሚቀየር ቢያውቅ ፥
- 17 ቢልዮን ብር ብድር ከንግድ ባንክ ማግኘት ቢችል ፥
- ያንን ብድር ወደ ዶላር በመቀየር 500 ሚልዮን ዶላር ማድረግ ቢችል ፥

ቴሌ ያለበት እዳ ስለ እሚታወቅ እና የቀረበት የዕዳ መጠን ለምሳሌ ፦ ከህዋዌ ፣ ኤርክሰን እና ዜድቲኢ ከተበደረው ብድር በ2024 የቀረበት መጠን 17 ቢልዮን ብር ስለ ነበር ፤ ያን 17 ቢልዮን ብር ፤ ለምሳሌ ከሐገር ውስጥ ተበድሮ ቢከፍል ኖሮ ፤ ሙሉ እዳውን ከፍሎ የ2025 ትርፉን በ5 ቢልዮን አሳድጎ 10.9 ቢልዮን ያደርሰው ነበር።

ያን ባለመድረጉ ግን ፤ በ2024 17 ቢልዮን የነበረው የእነ እዚኽ ሶስቱ ሻጮች እዳ ፤ 11.5 ቢልዮን ብር በክፍያ መልኩ ከተቀነሰበት በኋላ እንኳን ፤ ከመቀነስ ይልቅ ጨምሮ 29 ቢልዮን ብር ቀሪ እዳ ሆኖ ተቀምጧል።

	2025	2024
መነሻ ብድር	17,679,176,000	22, 132, 902,000
ቴሌ የሰበሰበው ወለድ	964,601,000	559,146,000
የወለድ ክፍያ	(9,496,956,000)	(5,892,016,000
ዋና (Principal) ክፍያ	(1,942, 952,000)	(692,801,000)
በምንዛሪ ለውጥ የጨመረ	22,610,782,000	1,571,944,000
ቀሪ	29, 814, 651,000	17,679,176,000

በጠቅላላውም ቴሌ በዶላር ያለበትን ዕዳ በትክክል ባለመስተዳደሩ ምክንያት ፤ በ2025 ብቻ በምንዛሪ ምክንያት ብቻ እዚኽ ጋር ከተጠቀሰው 22.6 ቢልዮን ጋር አብሮ በጠቅላላው 42 ቢልዮን ብር ከስሯል።

በነገራችን ላይ ቴሌ ፤ እንደ ኢትዮጵያ ባለ የውጭ ምንዛሪ በጣም ችግር በሆነበት እና ቴሌም ክፍያ የእሚሰበስበው በብር በሆነበት ሐገር ፤ በ3 እና በ4 ዓመታት የእሚከፈሉ ፤ በምንዛሪ መጠን ላይ ድርድር

ያልተደረገባቸው (Unhedged) እስከ 1.5 ቢልዮን ዶላር የእሚደርሱ ብድሮች መበደሩ ፤ የልማታዊ አካኼዱ የፈጠረው አንዱ እና ዋንኛው ተቋሙን የእሚያዳክም ምክንያት ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።

ስለ እዚኽ ፦ የቴሌን የገቢ እና የደንበኛ ቁጥር እድገት እያየን ከመደነቅ አልፈን ፤ ተቋሙ ገቢውን ወደ ትርፍ የእሚለውጥበትን አግባብ ማየት አለብን።

ያን ግዜ ቴሌ ገቢውን ሲያሳድግ የእሚያሳድግበት መንገድ ከምርታማነት ዕድገት በመነጨ ሳይሆን በሌሎች ገቢዎች ፣ በብድር ሽግሽግ እና በአንጻራዊነት ገቢውን ከእሚያሳድግበት ፍጥነት በላይ ያንን ገቢ ለማሳደግ የእሚያወጣውን ወጪ በማሳደግ መሆኑ ግልጽ ይሆን እና ቴሌ በተወሰነ ደረጃ ስኬታማ ነው ፤ ለስኬቱ የእሚያስከፍለው እና የእሚከፍለው ዋጋ በጣም ተቀባይነት የሌለው ነው እንድንል ያደርገናል።

ቴሌ የብቃት እና የተወዳዳሪነት ተምሳሌት ሳይሆን ፤ በመንግሥት እና መንግሥት በእሚፈጥራቸው ኹኔታዎች እየተከለለ እራሱን ተወዳዳሪ አምራች የእሚያስመስል መሆኑ ግልጽ ይሆናል።

2.4 የሥራ ማስኬጃ ክፍያ (Operating costs): በእየግዜው ከገቢው በላይ እያደገ ነው

በእዚኽ ክፍል የሥራ ማስኬጃ ክፍያ የተባለው ፤ የእሚከተሉት የአራቱ ድምር ነው ፡-

- ቀጥታ ወጪ (Direct Cost) ፥
- የሥራ ማስኬጃ ወጪ (Operating Expense) ፥
- ለደንበኛ አገልግሎት ተሰጥቶ ከአመት በላይ ክፍያው ባለመምጣቱ ኪሳራ የተባለ ፥
- ሌሎች ገቢዎች (ገቢ ሲሆን ተደምሮ) ወይንም ወጪዎች (ወጪ ሲሆን ተቀንሶ) ፥

ነው።

ከ2019 እስከ 2025 ባለው የሰባት ዓመታቱ የቴሌ ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ ስለ ቴሌ የአፈጻጸም ብቃት ትልቅ ነገር የእሚነግረን ፤ የቴሌ የሆነው ዓመት ዓመታዊ ገቢ ሳይሆን ፤ ይልቁንም ከገቢው አንጻር የሥራ ማስኬጃ ክፍያው ያደገበት አግባብ ነው።

ምክንያቱም ፡- ያ ኩባንያው በምን ያኽል ብቃት ገቢውን ወደ ውጤት እንደ እሚቀይር ስለ ዕሚያሳየን።

የእሚቀጥለው ሰንጠረዥ ቴሌ ከ2019 ጀምሮ ከገቢው አንጻር ፤ ለሥራ ማስኬጃ የከፈለውን ክፍያ እና ክፍያው ከገቢው አንጻር በእየ ዓመቱ ያሳየውን ጭማሪ ይዟል፡-

	ገቢ	የሥራ ማስኬጃ ክፍያ	ክፍያ ከገቢ አንጻር
2019	36,405,691,000.00	15,165,159,000.00	41.7%
2020	47,628,412,000.00	19,764,056,000.00	41.5%
2021	55,499,196,000.00	26,008,686,000.00	46.8%
2022	59,448,361,000.00	30,351,142,000.00	51.1%
2023	71,525,993,000.00	39,018,721,000.00	54.5%
2024	91,371,290,000.00	54,213,350,000.00	59.3%
2025	148,050,402,000.00	86,679,890,000.00	58.5%

እንደ ዕሚታየው ክፍያው በ2020 ከ2019 አንጻር የ0.2% ቢሆንም ቅናሽ ያሳየ ቢመስልም ከእዚያ በኋላ ግን ለተከታታይ አራት ዓመታት በጠቅላላው የ18% ጭማሪ ነው ያሳየው ፤ በ2021 ከ41.5% ወደ 46.8% ፣ በ2022 ከ46.8% ወደ 51.1% በመጨመር ፣ በ2023 ከ51.1% ወደ 54.5% በመጨመር ፣ በ2024 ከ54.5% ወደ 59.3% በመጨመር።

በ2025 ከ2024 አንጻር የ0.8% ቅናሽ ቢያሳይም ፤ ከ2021 በጠቅላላው ወደ 18% አከባቢ ጭማሪ ሲያሳይ የነበረ በመሆኑ ፤ ቅናሹ ብዙም አይደለም።

በጠቅላላው ካየነው በ6 ዓመት ውስጥ የሥራ ማስኬጃው ክፍያ በ17 ፐርሰንቴንጅ ፖይንት (percentage point) ጨምሯል።

በእነ እዚኽ ስድስት ዓመታት የቴሌ ገቢው አድጓል ፤ ገቢው ካደገበት ፍጥነት በላይ ግን የሥራ ማስኬጃ ክፍያው የበለጠ አድጓል።

ገቢ ከ36.4 ቢልዮን ወደ 148 ቢልዮን በማደግ ወደ 4.07 እጥፍ ሲያድግ ፤ የሥራ ማስኬጃ ክፍያ ከ15.2 ቢልዮን ወደ 86.7 ቢልዮን በማደግ በጠቅላላው በ5.72 እጥፍ ገደማ አድጓል።

ኩባንያው እየተስፋፋ እና እያደገ ነው ፤ በእያመቱ ባደገ ቁጥር ግን የአፈጻጸም ብቃቱ እያነሰ ነው።

ጤናማ ዕድገት በፍጹም ይኽን መምሰል የለበትም።

በማንኛውም በመደበኛ መንገድ በእሚቀሳቀስ የንግድ ተቋም ውስጥ ፤ በተለይ ደግሞ በቴሌኮም አገልግሎት ውስጥ የተሠማራ እና ቋሚ መሠረተ ልማቶችን ለአዳዲስ ተጠቃሚዎች በማቅረብ መሠረታዊ ወጪውን በእሚቀንስ (where fixed infrastructure costs can be spread across an expanding subscriber base) ፤ ዕድገት ወይንም አገልግሎት ማስፋት ፤ ከግዜ ወደ ግዜ ወጪን እየቀነሰ እንጂ እያባሰ መኼድ የለበትም።

ይኽ ዓይነቱ ከግዜ ወደ ግዜ እየተበረበረ እና እየተመናመነ የእሚኼድ የአፈጻጸም ብቃት የእሚያሳየን ነገር ቢኖር ፤ የልማታዊ አስተሳሰቡ ፤ ገቢን ሳያሳድግ አገልግሎት ማስፋት የእሚባል አባዜ ውስጥ እንደ አለ እና ከእዚኽም የተነሳ ፤ ተቋሙ ወጭው ቢያድግም ገቢው ግን በተመጣጣኝ መንገድ እያደገ እንደ አልሆነ እና ይኽም ኃብት ማባከን እንደ ሆነ ነው።

በቂ የሕዝብ ብዛት በሌለበት ቦታ የእሚገነባ ማንኛውም የሲግናል ማማ ፣ ዋጋውን በእማይመልስ መልኩ የእሚቀርብ እያንዳንዱ አገልግሎት ፣ ትርፋማነትን በእሚቀንስ መልኩ የእሚቀርብ እያንዳንዱ አገልግሎት የቴሌ የሥራ ማስኬጃ ክፍያ ውስጥ ገብቶ ቴሌን እየበረበረው ነው።

ሒሳቡ ለልማታዊ አስተሳሰብ ሲል አሠራሩን አይቀይርም ፤ አገልግሎት ብታሰፉም ገቢን ወደ ትርፍ የመቀየር አቅማችኹ ከዓመት ወደ ዓመት እየቀነሰ ነው ብሎ እየመሠከረ ነው።

ለንጽጽር ፤ ቴሌን ከሳፋሪኮም ጋር ብናስተያይ ፤ ሳፋሪኮም ቋሚ እና ተለወዋጭ ወጭዎቹን በመለየት ፤ እያንዳንዷን ጥሪ ፣ እያንዳንዷን ሜጋ ባይት ፣ እያንዳንዷን የገንዘብ ዝውውር ፣ ወዘተ ለመሸጥ ያወጣውን ወጪ ለማስላት ሲሞክር ፤ ቴሌ ቋሚ እና ተለወዋጭ ወጪዎቹን አንድ ላይ ደምሮ በማቅረብ ፤ አገልግሎት ለመስጠት የእሚወጡትን ተለዋዋጭ እና ቋሚ ወጭዎቹን በአግባቡ ዓያሳይም።

ከእዚያ ቀጥለን ፤ ኢቢትዳ (EBITDA – Earning Before Interest, Tax, Depreciation and Amortization) የእሚባለው እና አንድ የንግድ ተቋም የብድር ወለድ ፣ ግብር እና የእርጅና ዋጋ (Depreciation) ሳይከፍል በፊት ወይንም እያንዳንዱን ብር ገቢ ለመፍጠር የእሚያወጣውን የሥራ ማስኬጃ ክፍያ በመለካት የድርጅቱን የሥራ አፈጻጸም ውጤታማነት በእሚለካው (Which measures the operational efficiency of a company) መለኪያ መሠረት ፤ ገበያ በተሻለ ኹኔታ በእሚሠራበት እና ከባለአክሲዮኖች ቁጥጥር እና ጫና ያለበት የኬንያው ሳፋሪኮም እና ቴሌን ስናነጻጽር ፤ ለምሳሌ ፦ በ2025 ቴሌ የተሻለ ይመስላል።

2025	ሳፋሪኮም በሽልንግ ፤ በሚልዮን	ቴሌ በብር ፤ በሺ
ጠቅላላ ገቢ	**388,688.9**	**148,050,402**
ኢቢትዳ (EBITDA)	**172,150.9**	**74,445,420**
የትርፍ መጠን ከሥራ ማስኬጃ ወጪ በኋላ	**44.3%**	**50.3%**

ሆኖም ቴሌ እንደ እዚኽ ጠንካራ መስሎ የታየው በ2025 የገቢው 10% ገደማ የእሚሆን ሌሎች ገቢዎች (Other Incomes) የእሚል የ15.3 ቢልዮን ብር ገቢ ስለ አለው ነው። በእርግጥ ሳፋሪኮም ሌሎች ገቢዎች (Other Incomes) አለው ሆኖም የሳፋሪኮም የ2025 ከሌሎች ገቢዎች ያገኘው 4.2 ቢልዮን ሽልንግ ነው ከ388 ቢልዮን ጠቅላላ ገቢው አንጻር 1% ያደርገዋል የቴሌ 10% ሲሆን።

ሌሎች ገቢዎች መደበኛ የቴሌኮም አገልግሎት ከመስጠት ስለ እማይመጡ ፤ ከኹለቱም ካወጣናቸው ፤ የሳፋሪኮም የትርፍ መጠን ከሥራ ማስኬጃ ወጪ በኋላ (EBITDA Margin) 43.2% ሲሆን የቴሌ ግን ከ50.3% ባንድ ግዜ ወርዶ 39% ይሆናል።

$$\text{ሳፋሪኮም ኮር EBITDA Margin} = \frac{167{,}895.4}{388{,}688.9} = \mathbf{43.2}\%$$

$$\text{የቴሌ ኮር EBITDA Margin} = \frac{59{,}165{,}964}{148{,}050{,}402} = \mathbf{39.9}\%$$

ቀለል ባለ አነጋገር ፤ ሳፋሪኮም እያንዳንዱን ሽልንግ ገቢ ለመፍጠር ወደ 57 ሳንቲም ገደማ የሥራ ማስኬጃ ክፍያ ሲከፍል ቴሌ ባንጻሩ ወደ 60 ሳንቲም ይከፍላል ማለት ነው። ስለ እዚኽ ቴሌ 3 ሳንቲም የበለጠ የሥራ ማስኬጃ ወጪ አውጥቶ ነው አንድ ብር ገቢ የእሚፈጥረው።

እንደ እዚኹም ቀጥታ ክፍያ (Direct Cost) ከእሚባለው እና እያንዳንዱን አገልግሎት ለማቅረብ የእሚወጣውን ወጪ የእሚይዘውን የወጭ ዓይነት ይዘን ሳፋሪኮምን ከቴሌ ጋር ስነ አነጻጽር ፤ ሳፋሪኮም ገቢውን ከቀጥታ ክፍያው አንጻር ከፍ ያደረገ ሲሆን ፤ ቴሌ ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ ገቢው ሲያድግ የቀጥታ ወጪው ደግሞ በእሚያስደነግጥ መንገድ ነው የእሚያድገው።

ከ2021 እስከ 2025 ያለውን ዳታ ይዘን ስናነጻጽር ፤ ምንም እንኳን ቴሌ ገቢው በእዚኽ አምስት ዓመት ውስጥ በ160% በማሳደግ ጉድ ያስባለ ቢመስልም ፤ ቀጥታ ወጪውን በ781% በማሳደግ ጆሮ ጭው ያደርጋል። ተቋሙ ትልቅ ሆድ እና በጣም ቀጭን እግር እንደ አለው ሰው ፤ የኳሿኳር ህመምተኛ ነው እሚመስለው።

	2021	2025	ዕድገት በፐርሰንት
ቴሌ በብር			
ገቢ	55,499,196,000.00	148,050,402,000.00	166.76%
ቀጥታ ወጪ	6,593,213,000.00	58,131,009,000.00	781.68%
ሳፋሪኮም በሽልንግ			
ገቢ	264,026,500,000.00	388,688,900,000.00	47.22%
ወጪ	80,015,100,000.00	101,081,300,000.00	26.33%

እንደ እሚታየው ፤ ቴሌ የአንድ ጤናማ ተቋም የገቢም ሆነ የወጪ ዕድገት የለውም። እንደ ዕሚታየው በ5 ዓመታት ውስጥ የገቢ መጠኔ በ166% አደገ ሲል ፤ የቀጥታ ወጭዬ ደግሞ በ781% አደገ ይላል።

በአንጻሩ ሳፋሪኮም በእነ እዚኽ 5 ዓመታት ውስጥ ገቢው በ47% ሲያድግ ፤ የቀጥታ ወጭው በ26% ነው ያደገው።

ይኽ የሳፋሪኮም ዕድገት ፤ ከቴሌ አንጻር ገቢው ከቀጥታ ወጭው አንጻር ከፍተኛ ብልጫ ያለው መሆኑን ዓሳይቶ ፤ ሳፋሪኮም የገቢውን ዕድገት ገቢውን ለማስገባት ከእሚያወጣው ቀጥተኛ ወጪ በላይ በማድረግ የበለጠ ተወዳዳሪነቱን ከማሳየት ባሻገር ፤ ዕድገቱ ተገማች እንደ ሆነ ያሳያል።

በአንጻሩ ቴሌ ፤ የቀጥታ ወጭው የእሚያድግበት አግባብ ከገቢው አንጻር አራት እና አምስት እጥፍ መሆኑን በማሳየት ፤ ከፍተኛ የአፈጻጸም ክፍተት እንደ አለበት ከማሳየቱ ባሻገር ፤ ዕድገቱ ጤናማ እንደ አልሆነ እና የልማታዊነትን ስኬት ለማሳየት ፤ በከፍተኛ ወጪ ትልቅ ገቢ የማስመዝገብ እና ወጪውን በመሰወር ፤ ገቢውን እንደ ስኬት የማራገብ አባዜ አካኼድ ይመስላል።

በእርግጥ የ2024 የብር ምንዛሪ መዳከም የራሱን ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ፤ ከእዚያም በፊት ቢሆን ግን ፤ ለምሳሌ በ2021 እና በ2024 መካከል ብናይ ፤ የገቢ ዕድገቱም እንደ እዚኹም የቀጥተኛ ወጪ ዕድገቱ የአንድ ጤናማ ተቋም ዕድገት አይደለም።

	2021	2024	ዕድገት በፐርስንት
ቴሌ በብር			
ገቢ (Revenue)	55,499,196,000.00	91,371,290,000.00	64.64%
ቀጥታ ወጪ (Direct Cost)	6,593,213,000.00	25,606,800,000.00	288.38%
"ቋሚ" ወጪ (Operating Cost)	19,415,473,000.00	28,606,550,000.00	47.3%
ሳፋሪኮም በሽልንግ (Safaricom in KSH)			
ገቢ (Revenue)	264,026,500,000.00	349,447,300,000.00	32.35%
ቀጥታ ወጪ (Direct Cost)	80,015,100,000.00	97,046,900,000.00	21.29%
"ቋሚ" ወጪ (Operating Cost)	46,034,800,000.00	83,300,300,000.00	80.95%

እንደ እሚታየው ፤ ከ2021 እስከ 2024 ባሉት ዓመታት እንኳን ፤ ቴሌ ገቢውን በ64% በመቶ አሳድጎ (ብዙ ነው) ፤ ቀጥታ ወጪውን ደግሞ ከገቢው ዕድገት በላይ በ4.5 እጥፍ በ288% አሳድጓል። ስለ እዚኽ ተቋሙ ፦ የገቢን ዕድገት እንደ ዋንኛ የልማታዊነቱ ስኬት መለኪያ አድርጎ ፤ ያንን ለማሳካት ፤ ለምሳሌ፦ የቀጥታ ወጪውን ዕድገት ከእዚያ አራት እና አምስት እጥፍ እያደረገ እና የሥራ አፈጻጸሙን (Operational Efficiency) ከዓመት ዓመት እያደከመ ነው።

ቴሌ አገልግሎት እየሸጠ ሳይሆን ደንበኛ እየገዛ ነው እሚመስለው።

ምንም እንኳን ሳፋሪኮም በ2021 አከባቢ የኢትዮጵያን ገበያ ቢቀላቀልም እና ቋሚ ሊባሉ የእሚችሉት (Operating Expense) ወጪዎቹ በ2024 47.3% ዕድገት ካሳየው ቴሌ አንጻር በጣም ከፍ ብሎ የ80.9% ዕድገት ቢያሳይም ፤ በእዚኹ የግዜ መስኮት ውስጥ የቀጥታ ወጪው ግን 21% በመሆን 288% ዕድገት ካሳየው ቴሌ አንጻር በጣም ተወዳዳሪ ሆኖ ይታያል።

በቀላል አማርኛ ፤ ሳፋሪኮም የኢትዮጵያ ገበያን ለመቀላቀል ሲል በእነ እዚኽ አራት አመታታ ለኔትዎርክ ግንባታ ፣ የኮምሽን ክፍያ ፣ የሠራተኛ ቅጥር ፣ ወዘተ የእሚያወጣው ወጪ ከመደበኛው ግዜው በላይ በጣም ከፍ ቢልም ፤ አንድ ግዜ ቋሚ እሚባሉትን ወጪዎች ካወጣ በኋላ ፤ ገቢ ለመፍጠር የእሚያወጣው ቀጥተኛ ወጪ ግን ከመደበኛው ግዜ አንጻር ብዙ ሳይቀይር ፤ ገቢው ከሚያድግበት መጠን በታች ሆኖ እንዲቆይ በማድረግ ፤ ተወዳዳሪ አገልግሎት አቅራቢ መሆኑን አሳይቷል።

በሜዳዬ ነጥብ እንደ አልጥል ብሎ የፈራ የእሚመስለው ቴሌ ግን ፤ የሳፋሪ ኮምን ያኽል ባይሆንም ፤ በጣም አግሬሲቭ ሊባል የእሚችል እንደ ኔትዎርክ ማስፋፋያ ዓይነት የቋሚ ወጪዎችን ከማውጣት ባሻገር (47% ዕድገት አሳይቷል በእዚኽ ረገድ ያወጣው ወጪ) ፤ የቀጥታ ወጪው ግን ወደ 288% በማደግ ፤ አገልግሎት ከመሸጥ ይልቅ ደንበኛ እየገዛ አስመስሎታል።

ስለ እዚኽ ፡- በልማታዊ መንግሥት አስተሳሰብ የእሚመራው ቴሌ ፤ ገቢ እና ደንበኛ በማሳደግ ተከልሎ ፤ ያንን ግብ ለማሳካት ፤ እራሱንም ሐገርንም እሚያስከፍለውን ዋጋ እያበዛ ፤ አፈጻጸሙ ከግዜ ወደ ግዜ እየተሸረሸረ ነው።

2.5 ቴሌ በመስኩ ዝቅተኛ ምርታማነት አለው እሚባል ነው

ቴሌ በአንድ ሠራተኛ ምን ያኽል ግቢ እና ትርፍ ይፈጥራል ፣ ከኢንቨስትመንቱ ወይንም ከንብረት እና አንጡራ ኃብቱ አንጻር ምን ያኽል ገቢ ይፈጥራል ብለን ከመዘነው ፤ ደካማ እና ዝቅተኛ ምርታማነት ያለው ሆኖ ነው የእምናገኘው።

በ2025 ቴሌ 16,353 ሠራተኞች ነበሩት። በእዚያው ዓመት የተገኘውን 148 ቢልዮን ብር ገቢ ለሠራተኛው ቁጥር ብናካፍለው ፤ እያንዳንዱ ሠራተኛ በአማካይ 9.1 ሚልዮን ብር ገቢ ፈጥሯል ማለት ይቻላል ፤ ይኽም በ2019 ከነበረበት 2.1 ሚልዮን ብር አንጻር ከፍተኛ ዕድገት ነው።

ነገር ግን በሠራተኛ የተገኘ ገቢ ፤ ሠራተኛው ምን ያኽን ተንቀሳቅሷል የእሚለውን እንጂ በእንቅስቃሴው ልክ ምንያኽል እሴት/ቫልዩ ፈጥሯል ወይንም ጨምሯል የእሚለውን ዓያሳይም። በመሆኑ ፤ በሠራተኛ ከተገኘ ገቢ ይልቅ በሠራተኛ የተተረፈ ትርፍ ፤ የሠራተኛውን ምርታማነት ይለካል።

ስለ እዚኽ ፡- በ2025 ቴሌኮም በሠራተኛ ያተረፈውን ትርፍ ስናይ ፤ 354,000 ብር ሆኖ እናገኘዋለን። ይኽም በሰኔ 30 2025 አከባቢ የብር ምንዛሪ በዶላር 126 ገደማ ነው ብለን ብናሰላ ፤ እያንዳንዱ ሠራተኛ በዓመት 2,000 ዶላር ትርፍ አምጥቷል ማለት ነው።

ይኽን ከሳፋሪኮም ጋር እናነጻጽር። ሳፋሪኮም ዓመታዊ ሪፖርቱን የእሚሠራው በኬንያ ሽልንግ ቢሆንም ፤ የብር በገበያ ምንዛሪ እንዲሆን ከተወሰነ ወዲኽ ፤ የኬንያ ሽልንግ ከኢትዮጵያ ብር አንጻር የበለጠ ጠንካራ እየሆነ ነው። ለምሳሌ ፡- በፈረንጆቹ ግንቦት 20, 2026 አንድ ዶላር በ129 ሽልንግ ሲመነዘር ፤ አንድ ዶላር በብሔራዊ ባንክ ጨረታ ወደ 160 ብር ገደማ ደርሷል።

ስለ እዚኽ ፤ የኬንያውን ሽልንግ ሪፖርት እንደ ወረደ ብንቀበለው ፤ ምን አልባት ቴሌን አላግባብ ጠንካራ እናስመስለው ይሆናል እንጂ አላግባብ አንጎዳውም።

በመሆኑም ፡- የምንዛሪ ልዩነቱን በግዜያዊነት ትቼ ፤ ሪፖርቱ በብር እና በሽልንግ ቢሆንም ፤ ብር እና ሽልንግ እኩል ዋጋ እንደ አላቸው አድርጌ ነው ማቀርበው ፤ ምንም እንኳን አሁን ላይ ሽልንግ ከብር ቢጠነክርም።

ይኼን የቴሌን ሠራተኛ ትርፋማነት ፤ በ2025 በጠቅላላ 6,777 ሠራተኞች ከነበሩት እና በጠቅላላው 388 ቢልዮን ሽልንግ ገቢ ከነበረው እና 45.7 ቢልዮን ሽልንግ ካተረፈው ሳፋሪኮም ጋር ስናነጻጽር ፤ ሳፋሪኮም ከቴሌ አንጻር ብዙ እጥፍ ገቢ እና ብዙ እጥፍ ትርፍ እንደ አገኘ እናያለን።

2025	ቴሌ (ብር)	ሳፋሪኮም (ሽልንግ)	
ገቢ	148,050,402,000.00	388,688,900,000.00	
ትርፍ	5,794,409,000.00	45,757,200,000.00	
ሠራተኛ ብዛት	16,353.00	6,777.00	
ገቢ በሠራተኛ	9,053,409.28	57,354,124.24	6.3 እጥፍ
ትርፍ በሠራተኛ	**354,333.09**	**6,751,837.10**	19 እጥፍ

እንደ ዕሚታየው ፤ ምንም እንኳን ኹለቱም ነጻ ገበያ ውስጥ ቢኖሩ እና በሐገራቸው ገንዘብ ያገኙትን ገቢያቸውን እና ትርፋቸውን ወደ ዶላር ብንቀይር ፤ ሽልንግ ከብር እየጠነከረ በመምጣቱ ፤ የሳፋሪኮም የገቢ እና የትርፍ መጠን ትንሽ ከፍ ሊሉ ብችልም ልዩነቱ ጥቂት ነው ብለን እርሱን ትተን ፤ ብር እና ሽልንግ እኩል ምንዛሪ እንደ አላቸው አድርገን ፤ በሠራተኛ የተገኙ ገቢዎችን እና ትርፎችን ስናነጻጽር ፤ ሳፋሪኮም ከቴሌ ይልቅ ፤ በሠራተኛ 6.3 እጥፍ ገቢ ሲሰበስብ ፤ በሠራተኛ ያተረፈው ደግሞ ከቴሌ በ19 እጥፍ ይበልጣል።

ስለ እዚኽ ከምርታማነት አንጻር ፤ ሳፋሪኮም ቴሌን እጅግ እንደ እሚያስከነዳው ማየት ይቻላል።

ይኽ ማለት ፦ የቴሌ ሠራተኞች የግድ ከሳፋሪኮም ሠራተኞ ያነሰ ብቃት እና ችሎታ አላቸው ማለት አይደለም ፤ ወይንም ይኽ የግለሰብ ሠራተኞች ንጽጽር አይደለም ፤ ይልቁንም የመዋቅር ንጽጽር ነው።

በገበያ የእሚመራ መዋቅር እና በልማታዊነት የእሚመራ መዋቅር ንጽጽር ነው።

ለምሳሌ ፦ ሳፋሪኮም በ2025 በኢትዮጵያ ያለኝ የደንበኛ መጠን 9 ሚልየን ነው ሲል ፤ ከውጭ ካመጣቸው 100 ሠራተኞች ጋር ይኽንን ያኽል ደንበኛ ማግኘት እና ማገልገል የቻለው በ800 የሐገር ውስጥ ሠራተኛ በአጠቃላይ 900 የኢትዮጵያ ቅርንጫፉ ሠራተኞች ነው። ይኽም ማለት ፤ አንድ ሠራተኛ ለ10,000 ደንበኞች ገደማ ነው።

ቴሌ ዓመታዊ ሪፖርቱ ላይ የጠቅላላ ደንበኞቹን ቁጥር ባያስቀምጥም ፤ በዌብሳይቱ ላይ ያስቀመጠውን ስንወስድ ፤ ያም ማለት ከ2025 ሪፖርቱ አንድ ዓመት በኋላ የእምናገኘው የደንበኛ ቁጥር ወደ 83.2 ሚልዮን ደንበኞች እንደ አሉት ነው። ይኽንንም የደንበኛ ቁጥር ብዛታቸው 16,353 ለሆኑት ሠለራተኞቹ ስናካፍል ፤ ቴሌ በአንድ ሠራተኛ ወደ 5 ሺ ደንበኛ የእሚያገለግል ነው እሚመስለው።

ያም ማለት ፦ ሳፋሪኮም በአንድ ሠራተኛ የቴሌን እጥፍ ደንበኛ መፍጠር የቻለ ነው እሚመስለው።

በሌላ አገላለጽ ፤ ቴሌ በገበያ ስለ እማይመራ ፤ እያንዳንዱ የእምቀጥረው ሠራተኛ ምርታማነቴን ይጨምራል ? በእሚል አስልቶ አይሠራም ማለት ነው።

በገበያ ቢመራ ግን ከባለ አክስዮኖች ትርፋማነትን እና ተወዳዳሪነትን እንዲጨምር ጫና ስለ እሚኖርበት ፤ እንደ እሚመስለው አኹን የያዘውን ሠራተኛ በግማሽ ቀንሶ ፤ ተመሳሳይ ውጤት ማምጣት ስለ እሚችል ፤ ግማሽ ሠራተኛውን እንዲቀንስ ሊገደድ ይችላል።

የቀጠራቸው ሠራተኞች ከሳፋሪኮም ሠራተኛ ያነሰ ብቁ ስለ ሆኑ ሳይሆን ፤ ተቋሙ የወጪ ቅነሳ እና የትርፍ ጭመራ ጫና ስለ ሌለበት ፤ ከፍተኛ የሠራተኛ ቁጥር ተሸክሞ ፤ ምርታማነቱን በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል።

የቴሌ ዝቅተኛ ምርታማነት በሠራተኛ አጠቃቀሙ ብቻ ሳይሆን ፤ በኃብት አጠቃቀሙም የእሚታይ ነው።

ምንም እንኳን ቀደም ብለን እንደ አልነው ፤ በ2020 እና ከእዚያ በፊት በነበሩት ግዜያት ፤ ትክክለኛ የንብረት ዋጋ ስለ አልመዘገበ ፤ ከኃብት አጠቃቀም አንጻር በጥሩ ኹኔታ ትርፋማ እና አምራች የእሚመስልበት አጋጣሚ የነበረ ቢሆንም ፤ ያ ግን አንድ ግዜ ንብረቱ ኹሉ ከተገመተ በኋላ ፤ ትርፉ ከንብረቱ (Asset) እንዲኹም ከአንጡራ ኃብቱ አንጻር (Equity) አንጻር በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ነው የእምናገኘው።

ለንጽጽር ያኽል ፤ የቴሌን እና የሳፋሪኮምን የንብረት እና የአንጡራ ኃብት ትርፋማነት በ2024 እና በ2025 እናነጻጽር ፦

	ቴሌ 2025	ቴሌ 2024	ሳፋሪኮም 2025	ሳፋሪኮም 2024
ትርፍ ከንብረት አንጻር (ROA)	**1.74%**	**8.88%**	**8.88%**	**9.86%**
ትርፍ ከአንጡራ ኃብት አንጻር(ROE)	**5.70%**	**19.03%**	**20.43%**	**12.71%**

ምን አልባት በ2024 ቴሌ ፤ ከንብረትም ሆነ ከአንጡራ ኃብት ትርፋማነት አንጻር ከሳፋሪኮም ጋር ተወዳዳሪ የሆነ ሊመስል ይችላል። ቀደም ብለን ለማለት እንደ ሞከርነው ግን ፤ የ2024 ትርፉ ሌሎችች ገቢዎችን (Other Incomes) በማሳደግ እና የእዳ ሽግሽግ በማድረግ የመጣ ስለ ሆነ እና ይኽ ዓይነቱ የትርፍ ዕድገት ደግሞ ከአፈጻጸም ዕድገት ሳይሆን ፤ በሌላ መንገድ የእሚገኝ በመሆኑ ፤ እንደ ትክክለኛ የትርፍ መሻሻል የእሚታይ አይደለም።

በ2025 ትርፉ በከፍተኛ ደረጃ ወድቆ ትርፋማነቱ ከንብረትም ሆነ ከአንጡራ ኃብት አንጻር በጣም የቀነሱበት አግባብ ይኽንን ያረጋግጥልናል። እንዲያውም በ2025 ይኽን ያኽል አፈጻጸም ማስመዘገብ የቻለውም ፤ 15 ቢልዮን ያኽል ገንዘብ ከሌሎች ገቢዎች (Other Incomes) በማግኘቱ ነው።

በጠቅላላው ፤ ቴሌ ፦ በሠራተኛም ሆነ በንብረት አጠቃቀሙ ውጤታማ እሚባል አይደለም። ልማታዊነት በያከስርም የሠራተኛ ቁጥር ማብዛት ነው ካልተባለ እና ንብረት በእዳ ቢቦረቦርም ለቅዱስ ዓላማ ነው ካልተባለ ፤ የቴሌ ዝቅተኛ ምርታማነት ምንም ተቀባይነት የለውም።

በተለይ ደግሞ ፤ ገበያ በሐገር ደረጃ የተሻለ የሥራ ዕድል ሊፈጥር እንደ እሚችል እና ቴሌን በንብረት አምራችነቱን አሳድጎ ፤ ከቴሌ በላይ ልማታዊ ግብን ፤ እርሱም ፦ የኔትዎርክ ሽፋን እና አቅምን ያገናዘብ ተደራሽ የቴሌኮም አገልግሎት ማቅረብ እንደ እሚቻል ስናውቅ ደግሞ ፤ የአኹኑ የቴሌ አካኼድ ፍጹም ተቀባይነት አይኖረውም።

2.6 ቴሌ ከእያንዳንዱ ደንበኛ በአማካኝ ዝቅተኛ ገንዘብ ነው እሚሰበስበው

ቴሌ በ2025 83.2 ሚልዮን ደንበኞችን አገልግሎ 148.1 ቢልዮን ብር ገቢ አግኝቷል ፤ ይኸም ማለት በአመት ከእያንዳንዱ ደንበኛ 1,779 ብር ወይንም በወር ከእያንዳንዱ ደንበኛ 148 ብር አግኝቷል ማለት ነው።

ሳፋሪኮም ፤ በኢትዮጵያ እና በኬንያ 37.1 ሚልዮን ደንበኞችን ሲያገለግል ፤ ዓመታዊ ገቢው ወደ 388.6 ቢልዮን ሽልንግ/ብር ስለ ሆነ ፤ ከእያንዳንዱ ደንበኛ በአማካይ 10, 477 ብር ሰብስቧል ማለት ነው።

ይኸም ማለት ፤ ሳፋሪኮም ከቴሌ አንጻር ቢያንስ 6 እጥፍ ገቢ ከእያንዳንዱ ደንበኛ ሰብስቧል ማለት ነው ።

በእርግጥ ይኸ የቴሌን ደካማነት ብቻ አያሳይም ፤ ይልቁንም የኬንያ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይልቅ ከፍ ያለ ገቢ እንደ አለው እና ለምሳሌ ለስልክ እና ለኢንተርኔት በአማካይ ኬንያዊ ከአማካይ ኢትዮጵያዊ በ6 እጥፍ ማውጣት እንደ እሚችል የእሚያሳይም ነው።

ሆኖም 6 እጥፍ ልዩነት ግን በአንጻራዊ የኬንያ ሕዝብ የተሻለ ገቢ ብቻ የእሚገለጽ አይደለም ፤ ከእዚያ ውስጥ የተወሰነው ፤ ቴሌ በገበያ ቢመራ ኖሮ ከደንበኛው ይጠይቅ የነበረውን ክፍያ በግማሽ ወይንም ከእዚያ በላይ ቀንሶ ነው ዋጋ የእሚቀበለው ማለትም ነው።

በፐርሰንት እናስላው ካልን ፤ ቴሌ ከሳፋሪ አንጻር በአማካኝ ከእያንዳንዱ ደንበኛ የሳፋሪኮምን 16% ብቻ ክፍያ ተቀብሏል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኬንያ ሕዝብ አንጻር ዝቅተኛ ገቢ ስለ አለው ፤ ምንም እንኳን ቴሌ ዋጋውን ከሳፋሪኮም ጋር እኩል ያድርግ ባይባልም አኹን ካለበት 16% ትንሽ ከፍ አድርጎ የሳፋሪኮምን 30% ቢያደርገው ፤ በአመት ከአንድ ደንበኛ በአማካይ የእሚያገኘው ገቢ ከ1,779 ወደ 3,000–3,500 ያድግና ፤ የ2025 ገቢው የ148 ቢልዮን ሳይሆን ከ250 እስከ 290 ቢልዮን የእሚደርስ ይሆናል።

ስለ እዚኸ ፦ በግምት ፤ ቴሌ በ2025 ከደንበኞቹ ሊሰበስብ የእሚገባው የነበረ ፤ ነገር ግን ያልሰበሰበው ወደ 100 ቢልዮን ብር አለ ማለት ይቻላል።

አንድ የንግድ ተቋም ደግሞ ፤ በዓመት ወደ 100 ቢልዮን የእሚጠጋ እና ከደንበኞቹ መሰብሰብ ያለበት እና ያልሰበሰበው ገንዘብ ሲኖር ፤ ያ ክፍተት በመንግሥት ደግነት ወይንም የሕዝብ አቅም ማገናዘብ በእሚል የተተወ ሆነ አልሆነ ፤ ክፍተቱ መሞላት ስለ አለበት ፤ ተወደደም ተጠላም በአንድም በሌላ መንገድ ክፍተቱ መሞላቱ አይቀርም።

ከሒሳብ መዝገቡ እንደ እሚታየው ቴሌ ይኽን በልማታዊ አስተሳሰብ ምክንያት የእሚተወውን ፤ ለምሳሌ ፦ በ2025 ወደ 100 ቢልዮን ብር ሊጠጋ የእሚችል ገቢ ፤ የግድ መተካት ስለ አለበት የእሚያካክሰው ፤ በዋናነት በሶስት መንገድ ነው ማለት ይቻላል።

አንዱ መንግሥት በእሚያደርግለት "ስውር" ድጎማ ነው ፤ እርሱም፡- መሬት በነጻ በመስጠት ነው። ነገር ግን ቴሌ ከፍተኛ ዋጋ ያለው መሬት ከመንግሥት በነጻ ከተቀበለ በኋላ ፤ የግል ባለ አክሲዮኖች ስለ ሌሉት እና የሒሳብ አያያዙን በአግባቡ አድርጎ ይኽን በመንግሥት የተሰጠውን መሬት በዋጋው ንብረት ብሎ ስለ እማይመዘግበው ፤ ይኽ ልማዱ ፤ ቴሌን ከሆነው በላይ እጅግ ትርፋማ አድርጎ ሲያሳየው ነው የነበረው።

ለእዚያም ነው ከ2021 በፊት በአንጡራ ኃብት ያተረፍኩት ትርፍ (ROE) 80% እና ከእዚያ በላይ ነው እያለ ፤ ቴሌ ገንዘብ አታሚ ነው ሲያስብል የነበረው። ይኽ ግን የቴሌ ትርፋማነት ሳይሆን ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሬት ለቴሌ በነጻ ሰጥቶ ዋጋ ያስቀነሰበት ኃቅን ፤ ቴሌ ተጠያቂነት በሌለው የሒሳብ አያያዝ የደበቀበት ነበር።

2021 ላይ ወደ ገበያው ሳፋሪኮም ሲቀላቀል ፤ ቴሌ ሒሳቡን በአግባቡ የመያዝ ሕጋዊ እና ኢኮኖሚያዊ ግዴታ ውስጥ ሲገባ እና የሒሳብ መዝገቡ KPMG በተባለው የእንግሊዝ ኩባንያ ኦዲት ሲያደርግ ፤ ቴሌ ከመንግሥት በነጻ የተቀበለውን መሬት የግድ መመዝገብ ስለ ነበረበት ሲመዘግብ ፤ ትርፉን ወደ ኃብት በመቀየሩ ወይንም አዲስ ኢንቨስተር መጥቶ አዲስ ካፒታል ወይንም ኃብት ሳያስገባ ፤ የቴሌ ንብረት በአንድ ቀን በ82 ቢልዮን ብር ሲያድግ አብሮ አንጡራ ኃብቱም (Equity) በ71% አደገና ፤ ከ2021 በፊት በአንጡራ ኃብት ያተረፍኩት ትርፍ (ROE) 80% እና ከእዚያ በላይ የነበረው ትርፋማነት በእዚያው ምሽት ወርዶ 6% ገባ።

ቴሌ ከእላይ ሲታይ ፤ ለሕዝብ ብዬ በጣም ትንሽ ዋጋ እየሰበሰብኩ ነው ሊል ይችላል እና ያም የልማታዊነት ውጤት ነው ሊል ይችላል። ዕውነታው ግን የ82 ቢልዮን ብር መሬት በነጻ ወስዶ እና ያንን ደብቆ ነው። መሬቱ 82 ቢልዮን ብር ተብሎ የተገመተው በ2021 ነው ፤ ዶላር እና የዋጋ ግሽበት እንዲኽ በናረበት በ2025 ዋጋው ቢለካ መሬቱ ምን አልበት ዋጋው በእጥፍ ጨምሮ ሊሆን ይችላል።

ስለ እዚኽ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከቴሌ ርካሽ አገልግሎት በነጻ አገልግሎት አይደለም እያገኘ ያለው ፤ ይልቁንም ፤ ምን አልባት ሐገሪቱ በገበያ ብትመራ ፤ በገበያ በሊዝ ቢሰጠው ይበልጥ ሊጠቀምበት የእሚችለውን መሬት ለቴሌ በነጻ ሰጥቶ ነው።

አንድ መንግሥት የፈለገውን ያኽል ልማታዊ ቢሆን ፤ ከጠቅላላ ወጪው በላይ ደግ ሊሆን አይችልም ፤ ምክንያቱም ፦ ገቢ ከወጪ እያነስ ከኼደ ቴሌም ሆነ ለሌላ የልማት ድርጅት አገልግሎት በመስጠት ሊቆይ አይችልም። ችግሩ መንግሥት ግን ሕዝብ እና ሐገር የእሚከፍሉትን ዋጋ በእዚኽ መልኩ ስለ እሚሰውር ፤ መና እያወረደ ልማት እሚያስፋፋ ያስመስለዋል።

ዕውነታው ግን ፤ የሐገርን እና የሕዝብን ዕድል እያባከነ ፤ ለምሳሌ ፦ የቴሌ ዋጋ ቀነስኩ ነው እሚለው።

ለእዚያም ነው ቴሌ ፤ እንደ እዚኽ ዓይነት ፤ አንድ ግዜ ፤ ብር እሚያትም ፤ በሌላ ግዜ ደግሞ ሊከስር ጥቂት የቀረው ተቋም የእሚመስለው ፤ ምክንያቱም ፦ የገበያ ተጠያቂነት ስለ ሌለው ፤ የእሚፈጀውን ፍጆታ እና የእሚያመርተውን ምርት በግልጽ ስለ እማያሳይ።

ኹለተኛው ቴሌ ፤ የአገልግሎት ክፍያ ዝቅ በማድረጉ የእሚፈጥርበትን ጉድለት የእሚሸፍነው ፤ ከፍተኛ መጠን ያለው እና ምንም አይነት የምንዛሪ ድርድር ያልተደረገበት ብድር በመበደር እና በእየ ግዜው ያንን በማሸጋሸግ ነው።

ቴሌ ከዜድቲኢ ፣ ሁዋዌ እና ኤርክሰን (ZTE, Huawei and Ericsson) በአገልግሎት እና በመገልገያ መሣሪያዎች መልክ የተበደረው 1.5 ቢልዮን የአሜሪካ ዶላር ብድር ነበረበት (በሰሞኑ ማለትም ግንቦት 2018 አማካይ ምንዛሪ ወደ 243 ቢልዮን ብር ገደማ) ፤ ምንም እንኳን ከእዚያ ላይ ብዙውን ከፍሎ አኹን ያለበት የዕዳ መጠን በብር ወደ 29 ቢልዮን ብር ብቻ ቢሆንም።

ሲጀምር ቴሌ ፤ ከእላይ እንደ ተባለው ፤ እንደ ሳፋሪኮም እንኳን ባይሆን ፤ በገበያ ተመርቶ ከኢትዮጵያዊያን ገቢ አንጻር ተመጣጣኝ የሆነ የአገልግሎ ክፍያ ቢጠይቅ ኖሮ ፤ ለምሳሌ ፦ በ2025 ተጨማሪ 100 ቢልዮን ብር ገቢ ያገኝ ስለ ነበር ፤ በእዚኽ መልኩ በቂ የገንዘብ አቅም (Cash Fund) የእሚኖረው ኩባንያ ፤ አኹን ቴሌ እንደ እሚያደርገው ፤ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ችግር እና ከእርሱም ጋር ተያያዞ ቀጣይ የሆነ የምንዛሪ መዳከም ባለበት ገበያ ውስጥ እያለ ፤ ከ200 ቢልዮን ብር በላይ የእሚገመት የውጭ ምንዛሪ ብድር ፤ በእዚያ ላይ ፤ ይኽን ብድር እስኪያልቅ እምከፍለው በእዚህ ዓይነት የምንዛሪ መጠን ነው የእሚል ስምምነት በሌለው መልኩ አይበደርም ነበር።

አኹን ግን እንደ እዚያ ስለ አልሆነ ፤ ለምሳሌ ፦ በ2025 ካስገባው የ148 ቢልዮን ብር 41.4 ቢልዮኑን ለእዚኽ ብድር የወለድ እና የምንዛሪ መዳከም ክፍያ ነው ያዋለው ፤ ያም የገቢው 27% ፐርሰንት ገደማ ነው።

ሶስተኛው ፤ ቴሌ (የልማታዊነት ቅዠት) ይኽን ርካሽ አገልግሎት የእሚፈጥረውን ክፍተት የእሚሞለበት መንገድ ፤ በጣም ከፍተኛ መጠን ያለው የቴሌ አገልግሎት ለመንግሥት የሚንስትር መሥሪያቤቶች ፣ ለክልል መንግሥታት ፣ ለመንግሥት ዩኒቨርስቲዎች ፣ ወዘተ እና ለምሳሌ ለፋይዳ መታወቂያ ምዝገባ እና ሕትመት በመሸጥ ነው። ይኽ አካኼድ ሶስት ችግር ያለበት ነው ፦

1. የቴሌን የኢንተርፕራይዝ ሶሊሽንስ ፣ የክላውድ ሰርቪስ ፣ ወዘተ እንዲገዙ የእሚደረጉት የመንግሥት ተቋማት ፤ አስልተው እና ወጭያቸው ከጥቅማቸው አመዛዝነው ሳይሆን በትዕዛዝ ወይንም በግፊት ስለ እሚሆን ፤ አገልግሎቱ ከእሚጠቀሙበት ይልቅ ሊባክን ይችላል ፥
2. የመንግሥት ተቋማት ይኽን ምን አልባት 30% እንኳን በአግባቡ የእማይጠቀሙትን አገልግሎት የእሚከፍሉት ከግብር ወይንም በኢትዮጵያ ስም ከእሚመጣ የእርዳታ ገንዘብ በመሆኑ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ዋጋውን በአንድም በሌላም መንገድ የእሚከፍለው ፥

3. ብዙ ግዜ ፤ አገልግሎት ተጠቅመው ፤ ስለ እማይከፍሉ ፤ ለምሳሌ ፦ በ2025 ቴሌ አገልግሎት ሰጥቼ ፤ ክፍያ ባለማግኘት የከሰርኩት ብሎ ሪፖርት ያደረገው ወደ 2.2 ቢልዮን ብር አለ። በእየ ዓመቱም እንደ እዚያው ነው።

ስለ እዚኽ ስንጠቀልለው ፤ እንዲኽ ማለት እንችላለን ፦

➢ ልማታዊነት እንደ ተቋም ብቻ ሳይሆን እንደ ሐገር ስላደቀቀን ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኬንያ ሕዝብ አኳያ እንኳን ፤ በጣም ዝቅተኛ ገቢ ያለው ስለ ሆነ ፤ ብብዙ ኢንቨስትመንት የእሚቀርብለትን አገልግሎት እንኳን ገዝቶ መጠቀም በእማይችልበት ኹኔታ ላይ ነው።

➢ እዚያ ላይ ፤ የልማታዊነት ቅዠት ፤ እራሱ ያደቀቀውን ሕዝብ የመግዛት አቅሙ ደካማ ስለሆነ ፤ ዋጋ የቀነስ አገልግሎት አቀርባለኹ ብሎ ፤ ቴሌንም እንደ ተቋም ኩታራ ሲያደርግ ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፦

- መሬት ያለ ገበያ ለቴሌ በመስጠት ፥
- አበዳሪ ሳይሆኑ ኢንቨስተር ለእሚመስሉ አበዳሪዎች የሕዝብ ገንዘብ በመክፈል ፥
- የመንግሥት ተቋማትን በአግባቡ የእማይጠቀሙበትን አገልግሎት በሕዝብ ግብር እያስገዛ እና አንዳንዴም ክፍያ ባለመፈጸም ቴሌን በዓመት እስከ 2 ቢልዮን ብር እያከሰረ

ስውር ዋጋ እያስከፈለ ፤ በኢትዮጵያዊያን የባከነ ዕድል ፤ ደግ መስሎ ይታይበታል።

2.7 ቴሌ እሚቀበላቸው ስውር ድጎማዎች

እንደ እሚመስለው ፤ በልማታዊነት የእሚመሩ ተቋማት መታወቂያቸው ከእሚያመጡት ልማት ይልቅ በእሚወስዱት ድጎማ ነው።

ከእነ እዚኽ ድጎማዎች አንድ አንዶቹ ግልጽ ናቸው ፦ የበጀት ወጪዎች ወይንም በግልጽ መሰጠታቸው የታወቀ ስጦታ ሊሆኑ ይችላሉ። አብዛኛዎቹ ግን ስውር እና እማይታወቁ ናቸው።

ቴሌ የእሚቀበለውን ድጎማ ፤ የእሚከፍለው ሰፊው ሕዝብ ነው የእማያውቃቸው እንጂ ግልጽ ፣ ተጨባጭ እና ከፍተኛ መጠን ያላቸው ናቸው።

በእዚኽ ክፍል እነ እዚኽን ስውር ሰፊው ሕዝብ የእሚከፍላቸውን ዋጋዎች ዕናያለን።

2.7.1 ቴሌ እሚጠቀምበትን መሬት አልገዛውም ወይንም ዋጋውን በትክክል አላሰላውም

ቴሌ 5,605,567 ስኩዌር ሜትር የሆነ እና በጠቅላላ ወደ 560 ሔክታር የእሚለካ መሬት በመላ ኢትዮጵያ ከመንግሥት በነጻ ተቀብሏል።

ይኸን ያኽል መሬት ግን ፤ በቴሌ ሒሳብ ደብተር ላይ ፤ ከሕዝብ ያገኘውን ድርጎ ወይንም ደግሞ በንብረትነት በእጁ ላይ ያለውን ኃብት በእሚያሳይ መልኩ ፤ በገበያ ዋጋው ሳይሆን ፤ በነጻ ስለ ተቀበለው ፤ መቀበሉን ብቻ ለማሳየት በእሚበቃ መልኩ ፤ በጣም በትንሽ ብር ነበር ተመዝግቦ ተቀምጦ የነበረው።

የኩባንያውን ሒሳብ እንዲመረምር በ2023 ግን KPMG የእሚባለው የእንግሊዝ ኩባንያ ሲቀጠር ነው ፤ መሬቱን በዋጋው እንዲተመን ያደረገው።

አተማመኑም ፤ በገጠር እና በከተማ መካከል ያለውን የዋጋ ልዩነት ከግምት ያስገባ እና አማካይ የተጠቀመ ነበር። በእዚኽም መሠረት አንዱን ካሬሜትር በ14, 392 ብር ሒሳብ አስልቶ ጠቅላላ ዋጋውን 83.7 ቢልዮን ብር አደረገው።

ይኸን መንግሥት ለቴሌ በነጻ የሰጠውን መሬት ዋጋ በብዙ መልኩ ልናነጻጽረው እንችላለን ፤ ለምሳሌ ፦ ከቴሌ የ2025 ትርፍ አንጻር 14 እጥፍ ነው።

ወይንም ደግሞ ከ2018 ዓም የኢትዮጵያ መንግሥት በጀት አንጻር ካየነው ፤ ለምሳሌ ፦ የ2018 የመከላከያን በጀት በ2 እና በ3 ቢልዮኖች ይበልጣል። ለማነጻጸር እንዲመች ፤ ከገንዝብ እና ኢኮኖሚ ምኒስተር ዌብሳይት ላይ በተገኘ መረጃ መሠረት ፤ የኢትዮጵያ የ2018 የአንድ አንድ ዘርፎች በጀት ምን እንደ እሚመስል ላስቀምጥ ፦

የበጀት ዝርዝር በከፊል	**2018**
ፍትሕ እና ደህንነት	43,329,914,182
መከላከያ	80,985,957,180
ግብርና እና ገጠር ልማት	64,510,702,525
ውኃ ኃብት እና ኢነርጂ	40,148,744,299
ትምሕርት	115,497,342,987

የእዚኽ ነጻ መሬት ጉዳይ በእዚኽ ብቻ አያበቃም።

የ2023ቱ መሬቱን 83.7 ቢልዮን ብር ዋጋ የሰጠው ግምት ፤ በሐገሪቱ ውስጥ የውጭ ምንዛሪ ፖሊሲ ለውጥ ከመደረጉ እና ከፍተኛ ከሆነው የዋጋ ግሽበት ጋር በተያያዘ ፤ አሁን ያ ዋጋ የመሬቱን ዋጋ በፍጹም አያንጸባርቅም።

መሬቱ በ2023 ከተመዘነ በኋላ፦ አስቤዛ ፣ የግንባታ ዕቃዎች ፣ ከውጭ የእሚገቡ ዕቃዎች እና ሪል ስቴቶች ዋጋቸው በእጅጉ ጨምሯል ፤ በመላ ኢትዮጵያ።

በ2024 እና በ2025 ዓመታዊ የዋጋ ግሽበት በአማካይ 25% ነበር ብለን ብንል ፤ የመሬቱ ዋጋ አሁን 83 ቢልዮን ሳይሆን 130 ቢልዮን ብር ይደርሳል። በእነ እዚያ ኹለት ዓመታት የነበረውን የዋጋ ግሽበት 35% ካደረስነው ዋጋው ወደ 152 ቢልዮን ይደርሳል።

ይኽም 47 ቢልዮን ወይንም የ68 ቢልዮን ብር ጭማሪ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ይኽን ያኽል ገንዘብ ቴሌን እየደጎመው መሆኑ ግን ተገቢውን ሽፋን አላገኘም።

ሌላው ደግሞ መሬቱ በ2023 ዋጋ ሲወጣለት ፤ አንድ ዶላር በ57 ነበር የእሚመነዘረው ፤ በሰኔ 30 2025 አከባቢ የአንድ ዶላር ዋጋ ወደ 130 ገደማ አድጓል። ይኽም በመሬቱ የዶላር ዋጋ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ እንደምታ አለው።

ምክንያቱም ምንም እንኳን መሬቱ በብር ምንዛሪ ፖሊሲ ለውጥ ምክንያት ዶላር ሲወደድ ፤ የብር ዋጋው በጣም ቢጨምርም እና በ2023 83 ቢልዮን ብር የነበረው መሬት በ2025 ወደ 130 ቢልዮን ብር ሊያወጣ ቢችልም። በዶላር ስናሰላው ግን ፤ የዶላር ምንዛሪ በ2023 ወደ 57 ብር ገደማ ስለ ነበር ፤ መሬቱ የዶላር ዋጋው 1.47 ቢልዮን ዶላር ነበር።

2025 ላይ የዶላር ዋጋ 130 ብር ነበር ብለን አስበን እና መሬቱም በወቅቱ ዋጋ ወደ 130 ቢልዮን ብር አድጓል ብንል የዶላር ዋጋው 1 ቢልዮን ብር ገደማ ነው እሚሆነው ፤ ቢያንስ የግማሽ ቢልዮን ዶላር ቅናሽ አሳይቷል።

ስለ እዚኽ ፦ ለምሳሌ ፦ ቴሌን ለውጭ ኩባንያ በከፊል ለሽያጭ እናቅርበው ቢባል ፤ ቴሌ ዋጋው በዶላር ሊቀንስ ይችላል።

ሌላው ሶስተኛው ነጥብ ፤ የቴሌ ንብረት በዓመት የእሚያድግበት መንገድ ነው። ለምሳሌ ፦ በ2024 214 ቢልዮን የነበረው ጠቅላላ የንብረት መጠኑ በአንድ ዓመት ከ100 ቢልዮን ብር በላይ አድጎ 331 ደርሷል በ2025። ይኽ ወደ 117 ቢልዮን ገደማ ጠቅላላ ዓመታዊ ጭማሪ ግን የቴሌ ንብረት ከመጨመሩ የመጣ አይደለም።

መሬቱ በKPMG በ2023 በተገመተበት ዋጋ ላይ ነው ያለው።

በእዚኽ መልኩ የቴሌ የንብረት ዋጋ ያደገው ፦ በዶላር የገዛቸው የኔትዎርክ ዕቃዎች እና በዶላር የእሚቀበላቸው የአገልግሎት ክፍያዎች ፤ በብር በመተርጎማቸው ነው።

ይኽ ግን የንብረት ዕድገት አይደለም ፤ በብር መርክስ ምክንያት በዶላር የተገዙ ንብረቶች ያሳዩት የዋጋ ግሽበት ውጤት ነው። ይኽም ማለት የድርጅቱ የንብረት ዕድገት ባሕሪ ከድርጅቱ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ጋር ያልተያያዘ እንዲሆን ያደርገዋል።

እነ እዚኽን ሰብስበን ስናያቸው ፤ የቴሌ ባላንስ ሺት የዶላር መጠኑ የተጋነነ ፣ የብር መጠኑ ዝቅ የተደረገ ሆኖ ፤ የተቋሙ ሒሳብ እና ቁመና ፤ ገለልተኛ በሆነ እና ግልጸኝነትን ሊያረጋገጥ በእሚችል ተቋም ካልተመረመረ ፤ የድርጅቱን ትክክለኛ ቁመና ለመረዳት አስቸጋሪ ያደርጉታል።

አሁን ቴሌ የእሚከተለው የልማታዊ እሳቤ ግን እንዲህ ዓይነቱን ገለልተኛ የሒሳብ ምርመራ የእሚፈልግ እና የእሚፈቅድ አይደለም።

እንደ እሚመስለው ፤ ቴሌ ከመንግሥት በነጻ የተቀበለውን ይኽን መሬት ፤ አይደለም በሙሉ ዋጋው በግማሽ የገበያ ዋጋው ቢገዛው እንኳን ፤ ሊከስር እና ሊዘጋ የእሚችል ይሆናል። ካልሆነም ፦ በሌለው አቅም አጉል ደግ የእሚሆንበትን አካኼድ አቁሞ ፤ እራሱን በትርፍ ለመሥራት ያስገደዳል።

በጠቅላላው ቴሌ ፦ በስም አድጌያለኹ የእሚል ፤ በዕውነት ግን ከግዜ ወደ ግዜ ዋጋው እየቀነሰ እና ይኽም በዕድገት ስም የእሚቀንስ ዋጋ ለሕዝብ ያልተገለጸበት ፤ የልማታዊ መንግሥት ቁማር ይመስላል።

አብሮም መሬቱ ለምሳሌ በ2025 በዋጋው ቢሰላ ፤ የንብረት እና የአንጡራ ኃብት መጠኑ በጣም ስለ እሚጨምር ፤ ትርፋማነቱ ከንብረት እና ከአንጡራ ኃብት አንጻር በጣም ሊቀንስና ፤ ኩባንያው አሳሳቢ የሆነ የአፈጻጸም ችግር ውስጥ እንደ አለ ሊያሳይ ይችላል (Land Revaluation might result in a significant ROE and ROA decline)።

2.7.2 በዓመታዊ ሪፖርቱ ውስጥ የደሞዝ ክፍያው ከተመሳሳይ ተቋማት ጋር አልተነጻጸረም

በ2025 ኦዲትድ ሆኗል ተብሎ የጸደቀው የቴሌ ዓመታዊ ሪፖርት ፤ ስለ ደሞዝ በዝርዝር በእሚያወራበት ኖት 26 በእሚባለው ክፍል ላይ ለ16, 353 ሠራተኞቹ የአከፋፈለውን ደሞዝ አስቀምጧል። ይኽን የዶሞዝ አከፋፈል ሪፖርት በጥንቃቄ አይቶ በትክክል መተርጎም ያስፈልጋል ፤ ምክንያቱም ፦ እላይ ከእሚታየው በላይ የእሚገልጸው ነገር ስለ አለው።

እንደ ዓመታዊ ሪፖርቱ ፤ ቴሌ በ2025 ለ16, 353 ሠራተኞቹ ለደሞዝ እና ተያያዥ ጥቅሞች የከፈለው በጠቅላላ 15.96 ቢልዮን ብር ነበር።

ይኽንም ለጠቅላላው የሠራተኛ ቁጥር ብናካፍለው እና ቴሌ በአማካኝ ለአንድ ሠራተኛ በወር ስንት ብር ከፍሎ ነበር ብንል ፤ በ2025 ቴሌ ለአንድ ሠራተኛ በወር በአማካኝ 81,300 ብር እንደ ከፈለ ዕናያለን።

በእርግጥ ይኽ አማካኝ 81,300 ብር ውስጡ ግሮስ ሳላሪ ብቻ ሳይሆን ፤ ሌሎች እንደ አሎዋንስ ፣ ቴሌ ለሠራተኞቹ የእሚያደርገውን የጡረታ መዋጮ ፣ የጤና ኢንሹራንስ ፣ ቦነስ እና የኦቨር ታይም ክፍያ ስናወጣ ፤ እያንዳንዱ ሠራተኛ በአማካይ በወር የተከፈለው ግሮስ ሳላሪ ወይንም ጠቅላላ ደሞዝ ወደ 60, 600 ብር ይመጣል።

ይኽን ዓይነት ወርኃዊ ደሞዝ በኢትዮጵያ የሥራ ገበያ ውስጥ በጣም መልካም የእሚባል ደሞዝ በመሆኑ ፤ ቴሌ ከመሠል ተቋማት አንጻር ለሠራተኞቹ ዝቅተኛ ደሞዝ ነው እሚከፍላቸው ብሎ ከመተቸት በፊት ፤ ይኽን የአማካይ ክፍያ በጥንቃቄ መመርመር ይፈልጋል።

በእዚያ የደሞዝ ክፍያ ዝርዝር ባሳየበት ኖት 26 በእሚባለው ክፍል ላይ ፤ የደሞዝ ምድብ ሲያስቀምጥ ፤ ከ16, 353 ሠራተኞቼ ውስጥ 16, 352ቱ በዓመት ከሞቶ ሺ ብር በላይ ሲከፈላቸው ፤ አንድ ሠራተኛዬ ግን በዓመት ከ100 ሺ ብር በታች ይከፈለዋል ብሎ ይላል።

የእዚኽ የደሞዝ ምድብ አዘራዘር ፤ የቴሌን የደሞዝ አከፋፈል ዝርዝር እንዴት እንደ እሚደብቅ እና ምን ያኽሉ ሠራተኛ ምን ያኽል ብር እንደ እሚከፈለው እንደ ዕማያሳይ ለኹላችንም ግልጽ ይመስላል።

ሆኖም ከጠቅላላ 16, 353 ሠራተኞቼ ከአንዱ በስተቀር ኹሉም በዓመት ከ100 ሺ ብር በላይ ይከፈላቸዋል የእሚለውን ሪፖርት ይዘን ብንነሳ ፤ በቴሌ የደሞዝ መዝገብ ውስጥ በወር የመጨረሻ ትንሽ ወርኃዊ ደሞዝ የእሚከፈለው ሰው ፤ ጠቅላላ ደሞዙ 8, 333 ብር ገደማ ነው እንድንል ያስችለናል።

ይኽ ዓይነቱ ዝቅተኛ የደሞዝ መጠን ምንም እንኳን እያንዳንዱ ሠራተኛ ተገቢውን ክፍያ አግኝቷል ባያስብልም ፤ ለአንድ ልማታዊ ድርጅት ግን ጥሩ መነሻ ይመስላል።

ነገር ግን ፤ ይኽ የቴሌን ዕውነተኛ የደሞዝ አከፋፈል ዝርዝር አይነግረንም ፤ ምክንያቱም አማካኝ ደሞዙ በጣም ጥቂት የሆኑ ኢንጂነሮች እና የማኔጅመንት ሰዎች በእሚከፈላቸው ከፍተኛ ክፍያ ምክንያት ፤ አማካዩ ፤ ተገቢውን የቴሌን አማካይ ደሞዝ አያሳይም።

አንድ የመስክ ቴክንሺያን ወይንም የሽያጭ ወኪል ምን አልባት ወርኃዊ ደሞዙ ከ15,000 እስከ 25,000 ብር ሊሆን ይችላል። ምን አልባት አንድ የኔትዎርክ ኢንጅነር ደሞ ደሞዙ ከ35,000 እስከ 60,000 ሊሆን ይችላል። የመመሪያ ኃላፊዎች እና ከፍተኛ ማኔጀሮች ፤ ምንም እንኳን በጣም ጥቂት ቢሆኑም ፤ ምን አልባት ከ300, 000 ብር በላይ በወር ሊከፈላቸው ይችላል።

ስለ እዚኽ አማካይ የቴሌ ሠራተኛ ደሞዝ 60, 600 ቢባልም ፤ ይኽ አማካይ ግን ጥቂት በሆኑ በጣም ትልልቅ ደሞዝ በእሚከፈላቸው ሰዎች የመጣ ይመስላል።

ጉዳዩን በአግባቡ መገመት እንደ አይቻል ፤ ከሐገሪቱ የደሞዝ ኹኔታ አንጻር ምንም ትርጉም በእማይሰጥ መልኩ በእሚከተለው መንገድ ነው ያስቀመጠው ፡-

ዓመታዊ የደሞዝ ክፍያ መደብ	**በ2025**	**በ2024**
10,000 – 30,000	0	0
30,001 – 50,000	0	1
50,001 – 100,000	1	3
ከ 100,000 በላይ	16, 352	16, 738

ኦዲተሮችም ጉዳዩን ሳይተቹ ማለፍ ነው የመረጡት።

አኹን በኢትዮጵያ ኹኔታ ፤ ከአሉኝ 16, 353 ሠራተኞች ከአንዱ በስተቀር ፤ ኹሉም በዓመት ከ100 ሺ በላይ ነው እሚከፈላቸው ብሎ ማለት ፤ ምን ዓይነት የደሞዝ አከፋፈል ግልጸኝነት ነው ?

ሆኖም ቴሌ ከኢትዮጵያ የደሞዝ ገበያ አኳያ ጥሩ ደሞዝ እንደ እሚከፍል ብዙም አያከራክርም ፤ ምክንያቱም አማካኝ ደሞዝ ከአብዛኛው የሐገሪቱ የመንግሥት ሠራተኛ በላይ ነው።

አንድ የፌደራል መንግሥት ሚንስትር ደሞዙ ከ30,000 እስከ 45, 000 ብር በሆነባት ፤ በመንግሥት ሆስፒታል ውስጥ የእሚሠራ አንድ የሕክምና ዶክተር ጠቅላላ ደሞዙ ከ12,000 እስከ 20,000 በሆነባት ሐገር ፤ እንደ እዚኹም አብዛኛው የመንግሥት ሠራተኛ ደሞዙ በ8,000 እና 15,000 መካከል በሆነባት ኢትዮጵያ ፤ ቴሌ ሠራተኞቹን በደሞዝ ጥሩ አድርጎ እያገለገላቸው ነው ማለት ይቻላል።

ስለ እዚኽ ቴሌ የሠራተኞቹን ደሞዝ ተጭኖ አውርዶታል ሲባል ፤ ቴሌ በኢትዮጵያ ገበያ ኹኔታ ፤ ዝቅተኛ ከፋይ ነው በእሚል አይደለም። ይልቁንም ፡-

አንደኛ ቴሌ በአመት በአማካይ በአንድ ሠራተኛ ስንት ብር ገቢ ያገኛል ብለን ስናይ ፤ በ2025 የእምናገኘው ቁጥር ወደ 9 ሚልዮን ብር ነው ፤ ያ አንድ የኔትዎርክ ኢንጂነር ለቴሌ ያመጣለት ገቢ በመሆኑ ፤

ቴሌ ሞኖፖሊ ሆኖ ገበያውን ለብቻው ለረጅም ግዜ በመቆጣጠሩ እንጂ ፤ ይኽ ከፍተኛ ኢንጂነር አኹን ከእሚከፈለው በላይ ደሞዝ ይገባው ነበር። ስለ እዚኽ ቴሌ ብቸኛ የመስኩ ሞኖፖሊ በመሆኑ ፤ የውድድር ገበያ ሊያስቀምጥበት ከእሚችለው የደሞዝ እርከን በታች እየከፈለ ፤ ልዩነቱን የትርፉ አካል ያደርገዋል።

ኹለተኛ ፤ ለንጽጽር ሳፋሪኮም በ2025 በአማካይ የከፈለውን ደሞዝ ብናይ ፤ የኢትዮ ቴሌኮምን 4 እጥፍ ደሞዝ እንደ ከፈለ እናያለን ፦

	ቴሌ በ2025	ሳፋሪኮም በ 2025
ጠቅላላ የሠራተኛ ብዛት	16,353.00	6,777.00
ጠቅላላ የሠራተኛ ክፍያ	15,960,724,000.00	29,055,000,000.00
በሠራተኛ በአማካይ በዓመት የተከፈለ	976,011.99	4,287,295.26
በሠራተኛ በአማካይ በወር የተከፈለ	81,334.33	357,274.61

ይኽ በቴሌ እና በሳፋሪኮም መካከል ያለ የደሞዝ ክፍያ መጠን ልዩነት የእሚያሳየን አንድ ነገር ቢኖር ፤ ቴሌ ሞኖፖሊ ባይሆን ኖሮ እና በገበያ ተወዳድሮ እሚሠራ ቢሆኖ ኖሮ ፤ ሞያተኛ ለመሳብ እና ለማቆየት መክፈል የነበረበት ደሞዝ ፤ አኹን ከእሚከፍለው ደሞዝ በአማካይ ከ4 እጥፍ በላይ መሆን ነበረበት የእሚል ነው።

ስለ እዚኽ ቴሌ ደሞዝ ይጨቁናል ሲባል ፤ አኹን የልማታዊነት አስተሳሰብ ከነገሰበት ፤ የኢትዮጵያ ገበያ አንጻር አይደለም። ይልቁንም ሐገሪቱ ከታሰረችበት የሶቅራጠስ ዋሻ ውስጥ ብትወጣ እና በገበያ ብትመራ ኖሮ ፤ ቴሌ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቆየት ሊከፍል ይገባው ከነበረው ደሞዝ አንጻር ነው።

ይኽ አንጻራዊ የደሞዝ ጭቆና የእሚፈጥረው ልዩነት ፤ በቴሌ ሠራተኞች ለቴሌ የእሚደረግለት ድጎማ ነው።

ስለ እዚኽ ፦ ቴሌ በኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት በወል ብቻም ሳይሆን በሠራተኞቹም ድጎማ እየተደረገለት ነው። እና ቴሌ ይኽ ኹሉ ድጎማ እየተደረገለት ፤ ለሕዝብ ብዬ የቴሌኮም አገልግሎት እንዴት በርካሽ እያቀረብኩ ነው ሊል ይችላል?

ምክንያቱም ፦ የቴሌ ሠራተኞች በገበያ ቢወዳደሩ ኖሮ በእሚያገኙት እና አሁን ያለገበያ ውድድር በእሚከፈላቸው ደሞዝ መካከል ያለውን ልዩነት ለቴሌ በድጎማነት እየሰጡት ነው።

እናም ልማት እማያመጣው ልማታዊ መንግሥት ፤ ኔትዎርክ ለማዳረስ ስል ዋጋ እየቀነስኩ ነው ቢልም ፤ ዋጋ በመቀነሱ ምክንያት የእሚፈጠረውን ክስረት ፦ ከሕዝብ እና ከመንግሥት ኃብት እንዲኹም ከሠራተኛ ጉልበት ወስዶ እየደጎመ ፤ አብሮም ለመንግሥት አገልግሎት "በግድ" በመስጠት እና በመሳሰሉት መንገዶች እየደጎመ ፤ ቴሌም ሕዝቡም ማደግ በእሚገባው ልክ እንደ አያድግ እያደረገ ነው ያለው።

2.7.3 ወደ አክስዮን ገበያ በይፋ መቀላቀል (The IPO) እና ለተከፈለ ክፍያ ምንም ዓይነት ኃብት አለማስተላለፍ

ቴሌ 10 በመቶ የድርጅቱን ድርሻ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሽያጭ አቅርቤያለኹ በማለቱ ፤ በጥቅምት 2024 እና በየካቲት 2025 መካከል ፤ 47,377 የኢትዮጵያ ዜጎች አንድ አክሲዮን በ300 ብር ሒሳብ ገዝተው ነበር። በእዚኽም ሽያጭ ቴሌ ወደ 3.21 ቢልዮን ብር ሰብስቧል።

ይኽም መልካም የእሚባል አካኼድ ነበር ፤ ተቋሙ እራሱን ለተጠያቂነት እና ለግልጸኝነት በማዘጋጀት ፤ ተወዳዳሪ ለመሆን አስቧል ያስብላል።

ሆኖም በሰኔ 30, 2025 ፤ ማለትም የአክስዮን ሽያጩ ተከናውኖ ካለቀ ከ8 ወራት በኋላ ፤ አንድም ዜጋ ለአክሲዮን ግዢ ብሎ በከፈለው ብር መሠረት የአክስዮን ባለቤትነት ሰርተፍኬት ማግኘት ግን አልቻለም። የኦዲት ሪፖርቱም ብዙም ማብራሪያ ሳይሰጥ ፤ ይኽ የሒሳብ ሪፖርት እስከ ተዘጋጀበት ሰኔ 30, 2025 ድረስ የቱ ሰው ምን ያኽል ሼር እንደ እሚያገኝ ("there is no allotment for share buyers until the reporting date 30 June 2025.") እና ያንንም የእሚያሳይ የባለቤትነት ማረጋገጫ አልተሰጠም ብሎ ነው ያለፈው።

በእነ እዚኽ 8 ወራት የብር ዋጋ በ117% ቀንሷል። ስለ እዚኽ ዜጎች የቴሌን ሼር ለመግዛት ያስገቡት ወደ 3.21 ቢልዮን ብር አኹን የመግዛት አቅሙ በስምንት ወር ውስጥ ከግማሽ በላይ ቀንሷል።

ምን አልባት ቴሌ እና ቴሌን በባለቤትነት በበላይነት የያዘው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ምን አልባት ፤ ለየትኛው ሰው ምን ያኽል ሼር እንደ እሚደርሰው ሊደለድሉ ይችላሉ። እስከ አኹን ግን ያን አለማድረጋቸው እና ብሩን ተቀብለው ዝም ማለታቸው ፤ ነገሩን በልጽ ያልተነገረ ድጎማ አስመስለውታል።

በሐገራቸው የስቶክ ገበያ ውስጥ ተሳትፈው ፤ እራሳቸውንም ሐገር መጥቀም የፈለጉ ፤ የሐገሪቱን ሚድል ክላስ ሰዎችም ጥርጣሬ ውስጥ እንዲገቡ አድርጓል።

ከእዚያ በተጨማሪ ኹኔታው የልማታዊ መንግሥት ያለበትን ግልጽ የሆነ የተጠያቂነት ችግር በግልጽ ያሳያል።

2.7.4 የቴሌኮም ገበያ በልማታዊነት በመታገቱ ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ የእሚከፍለው ዋጋ

ሌላው በከፍተኛ ደረጃ በሕብረተሰቡ ውስጥ በመሠራጨቱ ምክንያት ለመተመን የእሚያስቸግረው ለመኖሩ ግን ምንም ጥርጥር የሌለበት ድጎማ ፤ ቴሌ በገበያ ባለመወዳደሩ ምክንያት ፤ ከገበያ ዋጋ በላይ ከደንበኞቹ የእሚሰበስበው የአገልግሎት ክፍያ ፤ ቴሌ ከተገልጋዮቹ የእሚቀበለው ድጎማ ነው።

እንደ ቴሌ ያለ አንድ ሞኖፖሊ ፤ ምንም የገበያ ውድድር በሌለበት ኹኔታ ፤ የሕዝቡን አቅም ባገናዘበ መልኩ ነው የአገልግሎት ክፍያ ዋጋ እመቀበለው ብሎ የእሚሰበስበው ክፍያ ፤ ዕውነትም ቴሌ በትንሽ ትርፍ ብቻ ነው ያን ክፍያ እየሰበሰበ ያለው ወይንስ እንደ ማንኛውም ሞኖፖሊ ፤ ዋጋ እንደ አሻው እየጫነ ነው የእሚለውን ጥያቄ በእርግጠኝነት መመለስ አይቻልም።

የቴሌ ዋጋ በእውነትም ዝቅተኛ ነው ወይንም ዝቅተኛ ነኝ ቢልም ከፍተኛ ነው ፤ ዝቅተኛ ከሆነስ ለየትኞቹ ደንበኞቹ በጣም ውድ ለየትኞቹ ደንበኞቹ ርካሽ ፤ የእሚለው ጥያቄ ተገቢ የሆነ ውድድር ባለመኖሩ ምክንያት ባግባቡ መመለስ አልተቻለም።

የኢትዮጵያ የቴሌኮም ገበያ ውድድር ስለ ሌለበት ግልጸኝነት የሌለው ቢሆንም ፤ በዓለም ላይ ያለውን ልምድ ካየን ፤ በአንድ ሐገር የቴሌኮም መስኩ የገበያ ውድድር ሲኖረው ፦ ዋጋ ዝቅ ይላል ፣ ጥራት ይጨምራል ፣ ደንበኞችም በዝቅተኛ ዋጋ ጥራት ያለው አገልግሎት በማግኘት የበለጠ ተጠቃሚ ሆነዋል።

በአንጻሩ ደግሞ የእዚኽ ግልባጭ ማለትም ፤ የቴሌኮም ሞኖፖሊ ሲኖር ፤ በዘላቂነት ዋጋ ቀንሶ ጥራት ጨምሯል የእሚል ነገር ፤ በየትኛውም የዓለም ክፍል አልታየም።

በእዚያ ላይ ቴሌ ለ30 ዓመታት ገደማ (እንደ ገና በኮርፖሬሽን መልክ ከተቋቋመ ወዲኽ) ፤ በሐገሪቱ ብቸኛው የሐገሪቱ የቴሌኮም አገልግሎት አቅራቢ በመሆኑ ምክንያት ፤ መክፈል ከእሚገባቸው በላይ የከፈሉት ክፍያን ፤ በየትኛውም የሒሳብ መዝገብ ውስጥ ተመዝግቦ አይገኝም። እንደው ቀልጦ የቀረ ነው።

ያ ማለት ግን ፤ ይኽ ክፍያ አልነበረም ማለት አይደለም። ክፍያው ነበር ፤ መጠኑም ቴሌ ለብቻው ለ30 ዓመት በናኘበት ገበያ ውስጥ ሳፋሪኮም መጥቶ ፤ በሰሥት ዓመት ብቻ 9 ሚልዮን ደንበኛ በማግኘቱ ይታያል።

የሳፋሪኮም ደንበኛ ዕድገት ፍጥነት ያሳየው የሕዝቡን ጥራት ያለው በጥሩ ዋጋ የእሚቀርብ የቴሌኮም አገልግሎት ፍላጎት ፤ ሕዝቡ ለደካማ አግልግሎት ከገበያ ዋጋ በላይ ሲከፍል እንደ ነበር ምስክር ይመስላል።

3 ገበያ ምን ማድረግ እንደ እሚችል ያሳየው የሳፋሪኮም መስታወት

ምን አልባት ሰዎች ፤ ሳፋሪኮምን በማነጻጸሪያነት ወስደን ፤ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ስናነጽጸር ፤ ኢትዮጵያ ኬንያ አይደለችም ፤ አንድ በኬንያ የሠራ እና ውጤታማ የሆነ ልምድ በኢትዮጵያ ሊሠራ እና ውጤታ ላይሆን ይችላል ሊሉ ይችላሉ።

ይኽ ክፍል ይኽን ትችት እንዲኹ ዝም ብሎ ከማጣጣል ይልቅ ፤ አባባሉ የእሚገባውን ትኩረት ሰጥቶ ፤ በተለይ ደግሞ እንደ ቴሌው ኹሉ ሳፋሪኮምም ኦዲት የተደረገ አመታዊ ሪፖርት ስለ አለው ፤ በእዚኽ ኦዲት በተደረገ ሪፖርት ላይ በመመሥረት ፤ ሳፋሪኮም ውጤታማ የሆነበት የገበያ ሞዴል በኢትዮጵያ ውስጥ ይሠራ እንደ ሆነ ዕንመልከት።

3.1 የባለቤትነት ጉዳይ

ሰዎች ሳፋሪኮም እንደ ቴሌ የመንግሥት ንብረት ሳይሆን የግል ንብረት ነው ይላሉ።

ስለ እዚኽ፡- ስለ ሳፋሪኮም የባለቤትነት መዋቅር አንድ አንድ ነገሮችን እናንሳ።

እርግጥ ነው ሳፋሪኮም እንደ ቴሌ የመንግሥት ንብረት አይደለም።

የኬንያ መንግሥት በሳፋሪኮም ውስጥ ያለው ድርሻ 35% ብቻ ነው። ይኽ የ35% ባለቤትነት ድርሻ ትልቅ መጠን ነው ፤ ሆኖም የኩባንያውን አቅጣጫ መወሰን የእሚችል እና ሙሉ ተቆጣጣሪነት የእሚሰጥ አይደለም።

የሳፋሪኮምን የባለቤትነት መዝገብ ስናይ ፤ በሳፋሪኮም ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ የያዘው ቮዳኮም የእሚባለው ኩባንያ ነው። ይኽ ቮዳኮም የእሚባለው ኩባንያ እራሱ አብዛኛው ድርሻው የተያዘው ቮዳፎን በእሚባል ዓለም ዓቀፋዊ የቴሌኮም ኩባንያ ነው።

ሳፋሪኮም ለሽያጭ በዘረዘረበት በናይሮቢው የስቶክ ኤክስንጄንጅ (NSE) ውስጥ 44.4% ድርሻ ያለው እና በኬንያ ስቶክ ኤክስቼንጅ ውስጥ ትልቅ ድርሻ ያለው ነው።

የሳፋሪኮም የቦርድ አባላት የቦርድ አባላት በግሉ መስክ ተመርጠው የእሚሾሙ እና የተቋሙን የገንዘብ አቋም ለማጠናከር (fiduciary duties) ተግተው የእሚሠሩ ናቸው።

የተቋሙ ማኔጅመንት ፤ የእሚወስነውን ውሳኔ ኹሉ ገበያ የእሚሰጠውን ዋጋ እየተመለከተ በመሆኑ ፤ ኢንቨስተሮች ያላቸውን የገበያ ንባብ ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው።

በእዚኽ ጽሑፍ ውስጥ ከእምናነሳው ሙግት አንጻር ፤ ይኽ ከባለቤትነት መዋቅሩ ልዩነት የተነሳ የመጣው ፤ ሳፋሪኮም በአንጻራዊነት ከቴሌ ያለው ልዩነት ትልቅ ፋይዳ አለው ።

ምክንያቱም ፡- ሳፋሪኮም ሙሉ በሙሉ የመንግሥት ሳይሆን ነገር ግን መንግሥት ቀላል የእማይባል ድርሻ ኖሮት ፤ በገበያ ውስጥ እንደ ማንኛውም ሸቀጥ እየተሸጠ እና ተወዳዳሪ በሆነ መንገድ እየሠራ ፤ መንግሥት ተቋሙን የማስተዳደር ጫና ሳይኖርበት ነገር ግን ኢንቨስት ካደረገው ገንዘብ የእሚጠቀምበት ነው።

የኬንያ መንግሥት በእዚኽ መልኩ እየሠራ ማለትም የሳፋሪኮም ሙሉ ባለቤት ሳይሆን ይልቁንም 35% ድርሻ ብቻ በመያዝ ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ቴሌን መቶ በመቶ በባለቤትነት ይዞ ከእሚጠቀመው በላይ እየተጠቀመ ነው።

ሌላው ቢቀር ይኽ ፤ መንግሥት ቴሌን በባለቤትነት በልማታዊነት ከእሚመራ ይልቅ ለገበያ ቢከፍተው የበለጠ ተጠቃሚ ይሆናል ፤ የእሚለው ሙግት ብቻ ፤ ቴሌን ወደ ግል ለማዞር በቂ መከራከሪያ ነው።

ይኽን በዝርዝር ዕንመልከተው፡-

3.2 በ2025 የኬንያ መንግሥት የተሻለ ግብር እና የትርፍ ክፍፍል (Dividend) አግኝቷል

በ2025 የኬንያ መንግሥት በሳፋሪኮም ከነበረው የ35% ድርሻ ፤ መቶ በመቶ የቴሌ ባለቤት ከሆነው የኢትዮጵያ መንግሥት የተሻለ ለበጀት አገልግሎት የእሚውል ገቢ አግኝቷል።

በ2025 የኬንያ መንግሥት ከሳፋሪኮም ያገኘው ጠቅላላ ገቢ 38.3 ቢልዮን ብር ሲሆን ፤ 14.8ቱን ከትርፍ ክፍፍል ሲያገኝ ፤ 23.5 ቢልዮን ብሩን ደግሞ በግብር አግኝቷል።

በአንጻሩ በእዚኹ በ2025 የኬንያን ሕዝብ 2.5 እጥፍ ሕዝብ ባላት ኢትዮጵያ የብቸኛው ቴሌኮም አገልግሎት አቅራቢ የነበረው የቴሌ 100% ባለቤት የኢትዮጵያ መንግሥት ፤ የቴሌ ባለቤት ከመሆን ያገኘው ገቢ በጠቅላላው 16.2 ቢልዮን ብር ነበር ፤ 4.1 ከትርፍ ክፍፍል ሲያገኝ የቀረውን 12.1 ከግብር በማግኘት።

በንጽጽር ሲቀመጥ የኬንያ መንግሥት በ35% ድርሻ 100% ድርሻ ካለው የኢትዮጵያ መንግሥት ይልቅ 2.4 እጥፍ ገቢ አግኝቷል።

3.3 ተወዳዳሪ ላልሆነ ተጠቃሚነት የኢትዮጵያ መንግሥት እራሱ ላይ አላስፈላጊ ብዙ ጫና አምጥቷል

የኬንያ መንግሥት ይኽን የ2.4 እጥፍ ጥቅም ለማግኘት ፦ አዲስ ኢንቨስትመንት ማድረግ ፣ መሬት በነጻ መስጠት ፣ የውጭ ምንዛሪን በጉልበት መወሰን ፣ የተለየ የሕዝባዊ ተልዕኮ ጫና በቴሌ ላይ ማምጣት ፣ ወዘተ አልነበረበትም ፤ ይልቁንም እንደ ቴሌ የመንግሥት የነበረውን ኬንያ ቴሌኮም የተባለውን ድርጅት 65% በመሸጥ ፤ 35% ብቻ መያዝ ነው የነበረበት።

የኬንያ መንግሥት እንዲኽ በማድረጉ እና የኬንያ ቴሌኮምን የባለቤትነት ውቅር በመቀየሩ ያተረፈው ነገር ቢኖር ፤ በዓመት 38 ቢልዮን ብር ፣ እንደ ቴሌ ሳይሆን በእየገዜው እያደገ እና እየጨመረ የእሚኼድ አንጡራ ኃብት ፣ ፈጽሞ ከእዳ ነጻ መሆን እና ሳፋሪኮም ለእሚወስዳቸው ውሳኔዎች ምንም ተጠያቂ አለመሆን ነው።

በአንጻሩ ፤ እሚያጎብጠውን ቀንበር መሸከም ሥራ መሥራት የእሚመስለው የኢትዮጵያ መንግሥት ግን ፦ በ2021 ባለው ዋጋ 2023 ላይ ሲሰላ ወደ 83.7 ቢልዮን ብር ነጻ መሬት መስጠት ፣ የ30 ዓመት ሞኖፖሊ መፍጠር ፣ የሐገሪቱን እና የተቋማትን የዶላር ብድር መጠን የእሚደብቅ "በወታደራዊ" ቁጥጥር ሥር የሆነ የውጭ ምንዛሪ መጠን ማስቀመት፣ ፣ በእያንዳንዷ የሐገሪቱ አቅጣጫ ለእሚተከል የኔትዎርክ ማማ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ኃላፊነት መውሰድ ናቸው።

ልማታዊያኑ ምን አልባት ፤ መንግሥት በእዚኽ መልኩ የከሰረው ፤ የኔትዎርክ ሽፋንን ለማድረስ ባለው ቁርጠኝነት ነው ሊሉ ይችላሉ ። የኔትዎርክ ሽፋን እና የአገልግሎት ጥራትም ቢሆን ፤ የኬንያ ኹኔታ ከኢትዮጵያ በጣም የእሚሻል ሆኖ ነው የእምናገኘው።

በኬንያ ብዙ ከአንድ በላይ ሲም የእሚጠቀሙ ሰዎች በመኖራቸው ምክንያት ፤ የኬንያ ሕዝብ ከ100% በላይ የቴሌኮም አገልግሎት ተጠቃሚ ነው።

በኢትዮጵያም በእርግጥ ከፍተኛ የቴሌኮም መሥፋፋት አለ ፤ ከ78 ሚልዮን በላይ ደንበኞች አገልግሎት እያገኙ ፤ ሆኖም ዛሬም ግን በኢትዮጵያ በሚልዮን የእሚቆጠሩ የገጠር ነዋሪዎች ፤ ኔትዎርክ ማግኘት አይችልም።

በኔትዎርክ ጥራትም ብንኼድ ፤ በኬንያ ያለው የገበያ አሠራር ፤ የ4G ኔትዎርክ ሽፋንን 97% አድርሶታል። 5G በብዙ የኬንያ ከተሞች እየተስፋፋ ነው።

በአንጻሩ 4G በኢትዮጵያ የ70% ሽፋን ነው ያለው። ስለ እዚኽ ከ30% በላይ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ከ4G ኔትዎርክ ሽፋን ውጭ ናቸው።

በኔትዎርክ ፍጥነትም ኬንያ ከሰሐራ በታች ባሉ ሐገራት ብዙ ግዜ ከፍተኛ ደረጃ ነው የእምታገኘው። በኢትዮጵያ በከተሞች የኔትዎርክ ፍጥነት ጥሩ ቢሆንም ከኬንያ አንጻር ፤ በአብዛኛው ሽፋኑ በልልቅ ከተሞች የተወሰነ ነው ማለት ይቻላል።

በጠቅላላው ፤ በየትኛውም የልማት መመዘኛ ፤ ማለትም ፦ ተቋሙ እንደ ተቋም ካለው አፈጻጸም እና በሐገር ደረጃ ከእሚጫወተው ሚና አንጻር ቢመዘን ፤ በገበያ መመራት ለምሳሌ ፦ ሳፋሪኮምን እንደ ተቋም ከቴሌ በላይ አድርጎታል ፤ በሐገር ደረጃ በእሚጫወተውም ሚናም የተሻለ ሚና እንዲጫወት አስችሎታል።

3.4 የምርታማነት ልዩነት

በ2025 ሳፋሪኮም በጠቅላላ 6, 777 ሠራተኞች ነበሩት። ከሰጠው አገልግሎት በጠቅላላው በዶላር ሲመነዘር ወደ 2.86 ቢልዮን ዶላር የእሚሆነ 371 ሽልንግ ገቢ ሰብስቧል።

ከማስፋፊያ እና ከሥራ ማስኬጃ ወጪዎቹ በኋላ (EBITDA) 205.8 ቢልዮን ሽልንግ አትርፏል ፤ ይኽም ከግብር እና ከእርጅና (Depreciation) እንደ እዚኹም አገልግሎት ለማቅረብ ከእሚያስፈልጉ ወጪዎች በፊት የ55% ትርፍ ነው። ከአንጡራ ኃብት ትርፋማነት (ROE) አንጻርም የ20% ትርፋማነት አለው።

በእዚያ ዓመት ያከፋፈለው ትርፍም ወደ 48.08 ቢልዮን ሽልንግ ነው። ይኽን ማድረግ የቻለውም ፤ በኢትዮጵያ የኔትዎርክ ማስፋፊያ እና ሌሎች ወጪዎች ኖረውበት ነው ፤ በእዚያ ላይ በኢትዮጵያ የብር የመግዛት አቅም መዳከም የፈጠረው ችግርም ተጠቂ ነበር።

በእዚያው ዓመት ጠቅላላ የኢትዮ ቴሌኮም ተቀጣሪዎች ብዛት 16, 353 ነበር። ቴሌም በእዚያ ዓመት የ148.1 ቢልዮን ብር ወይንም የ1.18 ቢልዮን ዶላር ገቢ አግኝቷል።

ከማስፋፊያ እና ከሥራ ማስኬጃ ወጪዎቹ በኋላ (EBITDA) 74.4 ቢልዮን ብር አትርፏል ፤ ይኽም ከግብር እና ከእርጅና (Depreciation) እንደ እዚኹም አገልግሎት ለማቅረብ ከእሚያስፈልጉ ወጪዎች በፊት የ50% ትርፍ ነው። ከአንጡራ ኃብት ትርፋማነት (ROE) አንጻርም የ5.7% ትርፋማነት አለው። በእዚያ ላይ ከገቢው አንጻር ትርፋማነቱ 3.9% ነበር።

ተቅማጭ የእሚሆኑ ገንዘቦችን ካነሳ በኋላ ከትርፉ 70% ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ማስተላለፍ ስለ አለበት ፤ ወደ 4 ቢልዮን ብር አስተላልፏል።

በሠራተኛ ኢቢትዳ (EBITDA) ላይ ባለ እና የሥራ ማስፋፊያ እና የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች ብቻ በተቀነሱበት ገቢ በማመንጨት ደረጃ ካነጻጸርናቸው ፤ ሳፋሪኮም ከቴሌ በ14 እጥፍ ይበልጣል።

ሳፋሪኮም ትክክለኛ የሆነ የገበያ ውድድር የእሚፈጥረው ጫና ባለበት ኹኔታ ውስጥ ስለ ሠራ ፤ ምንም እንኳን በኢትዮጵያ ሰፊ የእሚባል የማስፋፊያ ፕሮጀክት ላይ ቢሆንም እና የኢትዮጵያ ብር የመግዛት አቅም በ117% በተዳከመበት በእዚያ ወቅት ፤ ይኽን ማሳካት የቻለው ፤ የቴሌን አንድ ሶስተኛ የእሚሆን ቁጣር ባላቸው በ6,777 ሠራተኞች ነው።

እነ እዚኽ እዚኽ ግባ የእማይባሉ የአፈጻጸም ልዩነቶች አይደሉም። ይኽን ዓይነት የአፈጻጸም የእሚውልደው ፤ አንዱ በገበያ የእሚመራ ተቋም በመሆኑ ለትርፋማነት እና ለምርታማነት ስለ እሚወዳደር ነው ፤ ሌላው ደግሞ ልማታዊ በመሆኑ ትርፋማነት እና ምርታማነት ኹለተኛ ግቦቹ ሆነው በተልዕኮ ስለ እሚመራ ነው።

ይኽ ልዩነት የቴሌ ማኔጅመንት ከሳፋሪኮም ማኔጅመንት ያነሰ ከመሆኑ የመጣ አይደለም። ይልቁንም ኹለቱ በተለያየ የማሕበረ ኢኮኖሚ እሳቤ በተቃኙ መዋቅሮች ውስጥ ስለ አሉ ነው።

ልዩነቱ ፦ ከፍልስፍናዊ ልዩነት የመጣ ፦ የአመራር መዋቅር ፣ የሽልማት እና የተጠያቂነት ስረዓት (incentive and accountability mechanisms) ልዩነት ውጤት ነው።

3.5 ሳፋሪኮም በኢትዮጵያ: ተመሳሳይ ገበያ - የተለያየ ሞዴል

ጥሩው ማነጻጸሪያ ፤ ሳፋሪኮም በኬንያ ቴሌ በኢትዮጵያ በእሚል ሳይሆን ፤ ሳፋሪኮም እና ቴሌ በኢትዮጵያ ገበያ በእሚል ነው።

ምክንያቱም ፦ ያ ኹለት በአንድ ትልቅ የማክሮ ኢኮኖሚ ኹኔታ ውስጥ ሆነው ነገር ግን በተለያየ ሞዴል ላይ የተገነቡ ተቋማት ፤ አንድ ዓይነት በብር የእሚከፍል ደንበኛ እያገለገሉ ያላቸውን ልዩነት ስለ የእሚያሳይ በመሆኑ።

ቀደም ብለን እንደ አልነው ፤ ሳፋሪኮም በኢትዮጵያ 898 ቋሚ ሠራተኞች አሉት። በጠቅላላው በ2025 ፤ 8.84 ሚልዮን ደንበኞች አሉት። ገቢው በእዚያው ዓመት በ35.3% አድጓል።

የሞባይል ዳታ ገቢው በ35.8% አድጓል። የኤምፔሳ (M-PESA) በእዚያው በ2025 ጀምሮ 1.21 ሚልዮን ደንበኞች ይዟል።

በ2024 የውጭ ምንዛሪ ፖሊሲ ሲቀየር ፤ የብር ምንዛሪ በመዳከሙ ፤ ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ትልቅ ምት ደርሶበታል። ምክንያቱም ፦ በውጭ ምንዛሪ የገዛቸው ዕቃዎች እና የእሚከፍላቸው ሠራተኞች ነበሩት። ከእዚኽም የተነሳ ፤ ከኦፕሬሽናል ኪሳራ በ2026 ወጣለኹ የእሚለውን የመጀመሪያውን ግምት በማሻሻል መውጫው ግዜ 2027 ብሎ እንዲያሻሽል አድርጎታል።

ዓመታዊ ሪፖርቱ ይኽን መሻሻል በግልጽ ነበር ያስቀመጠው። እንደ እዚኹም ፦ በውጭ ምንዛሪ ከእሚከፍላቸው ኮንትራክተሮቹ ጋር ያለውን ድርድር ፣ ለግንባታ እና ለኤሌክትሪክ ሥራዎች ከውጭ ኩባንያዎች ይልቅ የኢትዮጵያ ሰዎችን መጠቀሙን እና ኤክስፓትሪየት የእሚባሉ እና በውጭ ምንዛሪ የእሚከፈላቸውን ሠራተኞቹን ቁጥር መቀነስ እና ዋጋ የማሰተካከል ሥራ እንደ ሠራ በግልጽ አስቀምጧል።

ሳፋሪኮም እንደ እዚኽ ዓይነት ምላሽ መስጠት የቻለው በገበያ ስለ እሚመራ ነው። ፈጣን ፣ ተግባራዊ እና የድርጅቱን ትርፋማነት ለማስቀጠል ተብለው የተሰጡ ምላሾች ነበሩ።

በአንጻሩ የኢትዮጵያ ቴሌ ለእዚኹ ተመሳሳይ የብር አቅም መዳከም የሰጠው ምላሽ ግን ከሳፋሪኮም የተለየ ነበር ፡- የምንዛሪ መጠን ድርድር ስለ አልነበረው በምንዛሪ መዳከም ምክንያት 41.4 ቢልዮን ብር በውጭ ምንዛሪ ኪሳራነት መመዝገብ ፣ በዶላር ከእሚከፍላቸው ኮንትራክተሮቹ ጋር ምንም ዓይነት ድርድር አለማድረግ እንደ እዚኹም የብር ምንዛሪን መዳከም ከግምት ያስገባ ምንም ዓይነት የዋጋ ማስተካከያም አላደረገም።

ንጽጽሩ የችግሩ ግዝፈት እና መጠን አይደለም ፤ ኹለቱም አንድ እና ተመሳሳይ የሆነ የብር መጠን መዳከም ነው የገጠማቸው። ይልቁንም በተቋም ደረጃ የሰጡት ምላሽ ግን ፤ ኹለቱ ተቋማት የእሚመሩበትን ፍልስፍና እና ውጤቱንም የእሚያሳይ ነው።

ተጠያቂነቱ ለባለ አስክሲዮኖቹ የሆነ ኩባንያ ፤ ኮንትራቶቹን እንደ ገና ይደራደራል ፤ ዋጋ ያስተካክላል ምክንያቱም ፡- ህልውናው በእዚያ ላይ ስለ ተመሠረተ። በአንጻሩ ቀዳሚ ተጠያቂነቱ ለተልዕኮው የሆነ ተቋም ፤ ኪሳራውን ይውጠዋል ፤ ምክንያቱም የብር ምንዛሪ ቢለወጥም ተልዕኮው ስለ እማይለወጥ።

3.6 ጉዳዩ የባለቤትነት ዓይነት አይደለም ይልቁንም የአስተዳደር ዘዬው ነው

ቴሌን ከሳፋሪኮም ጋር ማነጻጸር የእሚያሳየን እና የእማያሳየንን ነገር በጥንቃቄ ማስቀመጥ ተገቢ ነው።

የቴሌ እና የሳፋሪኮም ንጽጽር አንድ የእሚያሳየን ነገር ቢኖር ፤ የግል ባለቤትነት በኹሉም መስክ ፤ ኹል ግዜ ከመንግሥት ባለቤትነት የተሻለ ነው ማለት አይደለም። ለምሳሌ ፡- የሲንጋፖር አየር መንገድ ሙሉ በሙሉ የመንግሥት ንብረት ነው ፤ ነገር ግን በዓለም ላይ ካሉ በጥሩ ኹኔታ ከእሚመሩ አየር መንገዶች አንዱ ነው።

እንደ እዚኹም የቦትስዋናው ዴብስዋና (Debswana) የተባለው የዳይመንድ ማዕድን አውጭ ድርጅት በአፍሪካ ውስጥ የስኬታማ መንግሥታዊ የልማት ድርጅት ጥሩ ምሳሌ ነው። ስለ እዚኽ ፡- ኹሉም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ስኬታማ እና ውጤታማ ሊሆኑ አይችሉም የእሚል በመረጃ ላይ የተደገፈ ድምዳሜ የለም።

ይልቁንም መረጃው የእሚያሳየው ፤ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች ፤ ለገበያ ውድድር ተጋልጠው ፤ የውድድር ጫና ሳይኖራቸው እና ገለልተኛ የሆነ አስተዳደር በመያዝ ለባለአክሲዮኖቻቸው ተጠያቂነት ሳይኖራቸው ሲቀር ፤ ያለ ምንም ጥርጥር ፡-

- የወጪ አወጣጥ እንዝህላልነት ፣

- የደሞዝ ጭቆና ፣
- ተገቢው ጥንቃቄ ያልተደረገባቸው ዕዳዎች እናም
- በርካታ ስውር ድጎማዎች የእሚሸከሙ ፤

የልማት ሳይሆን የኪሳራ ድርጅት እንደ እሚሆኑ ነው።

ስለ እዚኽ ጥያቄው ለኢትዮጵያ ፤ ቴሌ የመንግሥት ይኹን ወይንስ አይሁን አይደለም። ይልቁንም አሁን ተቋሙ ያለው አስተዳደራዊ ውቅር ፤ ማለትም ፡- 100% የመንግሥት የሆነበት ፤ ተጠያቂነቱ ለባለ አስክሲዮን ሳይሆን ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ የሆነበት ፣ ምንም ገለልተኛ ተቆጣጣሪ አካል የሌለው ፣ አክሲዮኑ በገበያ የእሚሸጥ ባለመሆኑ ዋጋውን ገበያ ያልወሰነለት ፣ የሒሳብ አያያዙ ተጠያቂነት የሌለበት ፣ ወዘተ ፤ ሆኖ መቀጠል ይችላል ወይንስ አይችልም ነው።

የሰባት ዓመታት የቴሌ መረጃ እና የ2025 ኦዲት የተደረገው ሪፖርት የእሚለው ፤ ይኽ አካኼድ በፍጹም መቀጠል አይችልም ነው።

4 የልማታዊያኑ መከላከያ — እና የማይሠራበት ምክንያት

ይኽ የልማታዊነት እና የገበያ ንጽጽር የእሚያደርግ ጽሑፍ ፤ ልማታዊያኑ የእሚያቀርቡትን እና አላቸው የእሚባለውን ሙግት ፤ በትክክል መዝኖ መልስ ካልሰጠ ዕውነተኛም ሙሉም አይሆንም።

የልማታዊያኑ ትክክል አይደሉም እንጂ ሙግታቸው ምላሽ የእማይገባው አይደለም።

ዋንኛ ሙግታቸውም ፡- እንደ ኢትዮጵያ ባለ ፤ የገበያ ክፍተት እንዲኹም የካፒታል እጥረት ባለበት እና የማሕበረ ኢኮኖሚ ተቋማት ደካማ በሆኑበት ሐገር ፤ የፖለቲካ አመራሩ ጥሩሱን ነክሶ ኪሳራ ለመዋጥ ቁርጠኝነት ካላሳየ ፤ ልዩነቱ የእሚሆነው ፤ ሕዝቡ የዘመናዊ ኔትዎርክ ተጠቃሚ መሆን እና አለመሆኑ ነው ብለው ስለ እሚያስቡ ነው።

ስለ እዚኽ ስጋታቸውን ዝም ብሎ ከማጣጠል ተገቢውን መልስ መስጠት ይገባል።

ልማታዊያኑ ቴሌን አኹን ባለበት ለማስቀጠል የእሚያቀርቧቸው ጠንካራ ሊባሉ የእሚችሉት ሙግቶቻቸው የእሚከተሉት ናቸው ፤ አራቱም ግን ጥሩ ምዘናን ተቋቁመው መቆም አይችሉም።

4.1 ገበያ ገጠሩን የኢትዮጵያ ክፍል አያገለግልም

ኢትዮጵያ በጠቅላላው የ120+ ሚልዮን ከእሚሆነው ሕዝቧ ከ75% በላይ የእሚሆነው በገጠር ስለ እሚኖር ፤ ይኽ የልማታዊያኑ ስጋት ትኩረት ተሰጥቶት ሊመለስ ይገባል።

ጥቂት የሕዝብ ቁጥር ባላቸው እና እንደ ኢትዮጵያ ተራራማ በሆነ ሐገር ለእሚኖሩ ለገጠር ነዋሪዎች የኔትዎርክ አገልግሎት መገንባት ፤ ብዙ ግዜ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት አይኖረውም። ስለ እዚኽ ፡- ለትርፍ የእሚሠራ እና የአሻውን እንዲያደርግ የተተወ የቴሌኮም ኩባንያ እንደ አዲስ አበባ ፣ ድሬዳዋ እና ሐዋሳ ያሉ ከተሞችን በደንብ አገልግሎ ሰፊውን የኢትዮጵያ አከባቢ ይተውዋል።

ሆኖም ለእዚኽ ችግር መልሱ መንግሥታዊ የቴሌኮም ሞኖፖሊ አይደለም። ይልቁንም ፤ ኹሉም ኢትዮጵያ ውስጥ ለመሥራት የቴሌኮም ፈቃድ የእሚያገኙ ኩባንያዎች ፤ በሕግ ፤ ትርፋማ ከሆኑ አከባቢዎች የእሚያገኙዋቸውን ገቢዎች ፤ የተወሰኑ ፐርሰንቱን ወስደው ፤ ዝቅተኛ ትርፍ ወይንም ምንም ትርፍ በሌላቸው አከባቢዎች የኔትዎርክ አገልግሎት ለማስፋፋት እንዲያውሉ ውል ማስፈረም ነው።

በሌላ አነጋገር የግል ቴሌኮም ካምፓኒዎች ፈቃድ ሲያገኙ ፤ ክሮስ ሰብሲዲ (cross-subsidy) በማድረግ ፤ ከትርፋማ አከባቢዎች የእሚያገኙትን የተወሰነ ገቢ ፤ ትርፋማ ያልሆኑ አከባቢዎችን እንዲደጉሙ በኢትዮጵያ የንግድ ፈቃድ ማግኛ ቅድመ ኹኔታ አድርጎ ማስፈረም ነው።

ይኽ ዓይነቱ አሠራር በብዙ የአፍሪካ ሐገራት ተሞክሮ ስኬት አስመዝግቧል።

የኬንያ የኮምኒኬሽን ባለስልጣን መሥሪያቤት የእሚያስተዳድረው ፤ የሐገር ዓቀፍ ሽፋፋን ማስፋፊያ ፈንድ (Kenya's Universal Service Fund) በእዚኽ መንገድ ፤ አዋጭ ባልሆኑ የሐገሪቱ ክፍሎች ኹሉ ኔትዎርክ ማዳረስ ችሏል ፤ የገበያ ተወዳዳሪነትን ሳያፈረስ።

የቴሌኮም ፈቃድ አሰጣጡን በውድድር በማድረግ እና የኔትዎርክ ሽፋን ማዳረስን ግዴታ አብሮ በማካተት ፤ በሩዋንዳም የተከተሉት ሞዴል በአፍሪካ ከፍተኛውን የሞባይል አገልግሎት ሽፋን አምጥቷል።

ጋና ፣ ታንዛኒያ እና ዩጋንዳም ፤ የገበያ ውድድር ማስቻል እና የኔትዎርክ አገልግሎት ተደራሽነትን ሐገር ዓቀፍ ማድረግ ፤ እማይታረቁ ስለ እዚኽ አንዱን እንድንመርጥ የእምንገደድባቸው እንደ አልሆኑ አሳይተዋል።

ይልቁንም መንግሥት ትክክለኛውን ፖሊሲ መቅረጽ እና በሥራ ላይ ማዋል ከቻለ ፤ የገበያ ውድድሩም የኔትዎርክ ሽፋኑም አብረው ሊሳኩ የእሚችሉ ናቸው።

በሐገር ውስጥ የእሚገኙ የቴሌኮም ፈቃዶች ፤ የኔትዎርክ ሽፋንን እንዲያስፋፉ ግዴታ ውስጥ ማስገባት ፤ የገጠሩን አከባቢ በኔትዎርክ የማያያዙን ተልዕኮ ከባለቤትነት ዓይነቱ ጋር ያለውን ትሥሥር በመበጠስ ፤ የቴሌኮም ተደራሽነት ለማስፈን የመንግሥት ባለቤትነት የግድ አስፈላጊ እንደ አልሆነ ያረጋግጣል።

መላ ኢትዮጵያን ፤ ገጠሩንም ጨምሮ በኔትዎርክ ማያያዝ ፤ ተከባሪ እና ሊያዝ የእሚገባው ተልዕኮ ነው። ይኽን ተልዕኮ ለማሳካት ግን ፦ አንድ ለእናቱ የሆነ እና ይኽን ተልዕኮ ለማሳካት በውጭ ምንዛሪ ብድር ሲወስድ የውጭ ምንዛሪ ሊፈጥርበት የእሚችለውን ችግር ከግምት የእማያስገባ የመንግሥት ቴሌኮም ካምፓኒ በመመሥረት ለማሳካት መሞከር ግን ብቸኛውም ትክክለኛውም መንገድ ግን አይደለም።

ትክክለኛው ዘዴ ፦ የኔትዎርክ ሽፋንን የማዳረስ ተልዕኮውን እንደ ያዙ ፤ የእሚሳካበት መንገድ በግልጽ በተወዳዳሪ የቴሌኮም ኩባንያዎች ላይ በእሚጣል የስምምነት ግዴታ ፤ የማስፋፊያ ወጪው ከመንግሥት ካዝና ሳይሆን ከትርፋማዎቹ ኩባንያዎች ገቢ ላይ በእሚታሰብ መልኩ እንዲሆን ማድረግ እና ታታሪው ገበያ ሲያሳካው ማየት ነው።

4.2 የቴሌኮም መስክ ከሐገር ደህንነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ነው

ይኸም እንደ ኔትዎርክ ሽፋን ፤ የእራሱ ፋይዳ ያለው ሙግት ነው። የአንድ ሐገር የቴሌኮምንኬሽን መሠረተልማት ሐገሪቷ ፦ በሐገር ውስጥም ሆነ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ግንኙነት የእምታደርግበት መንገድ ፣ የመረጃ ልውውጦቿ እና የተለያዩ የቅኝት ሥራዎች የእምትሠራበት (surveillance) ቴክኖሎጂ በመሆኑ ስትራቴጂካዊ ፋይዳው ከፍተኛ ነው።

የአንድ ሐገር መንግሥት እንደ እዚኽ ዓይነት ወሳኝ መሠረት ልማቶች ፤ በውጭ ኃሎች ምን አልባትም ፤ ለሌሎች የብሔራዊ ጥቅም ባላንጣዎች አገልግሎት ላይ ሊውል በእሚችል መልኩ ፤ እንዲያዝ አይፈልግም።

የእዚኽ ሙግት ችግሩ ፤ መንግሥት በደህንነት ስጋት ምክንያት የቴሌኮም መስኩን መቆጣጠር ካለበት ፤ በተመሳሳይ ሙግት ፦ ሆስፒታሎችንም ፣ የባንክ መስኩንም ፣ የምግብ ማምረት እና ማከፋፈል መስኩንም መቆጣጠር አለበት ፤ ምክንያቱም ፦ እነርሱም በተመሳሳይ ለሐገር ደህንነት በጣም አስፈላጊ በመሆናቸው።

በተጨማሪም ፦ መንግሥት ያሉበትን የደህንነት ስጋቶች ለማስወገድ ፤ የቴሌኮም መስኩን በንብረትነት መያዝም የለበትም።

ከደህንነት አንጻር ካየነው ፤ መንግሥት የእሚያስፈልገው ፤ መስኩን ከደህንነት አንጻር የእሚቆጣጠርበት እና ለደህንነት ሲባል ጣልቃ ሊገባ የእሚችልበት አሠራር ነው የእሚያስፈልገው።

ታላቋ ብሪታንያ ፤ ለቴሌኮም ኩባንያዎች የንግድ ፈቃድ ስትሰጥ በእምታስቀምጠው ግዴታ አማካኝነት ፤ ከደህንነት አንጻር ቁጥጥር ማድረግ እና ቅኝት ማድረግ እንደ እምትችል በማስቀመጥ ፤ የብርትሽ ቴሌኮም ባለቤት ሳትሆን የደህንነት ስጓቷን አስወግዳለች።

ፈረንሳይ በአንድ ወቅት ፤ ኦሬንጅ በእሚባለው የቴሌኮም አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት ውስጥ ፤ ምንም እንኳን መንግሥት ወደ 13% ብቻ የእሚሆን አናሳ ድርሻ ቢኖረውም (በኢንቨስትመንት ባንኩ ካደረገው ውጭ) ፤ በፈቃድ አሰጣጡ ወቅት ፤ ወርቃማ የእሚባል አክሲዮን (Golden Share) ለእራሱ በመስጠት በወሳኝ ጉዳዮች ላይ ድምጽ በድምጽ የመሻር መብት (Veto) ሰጥቶ ነበር።

ምንም እንኳን አሁን ያንን አሠራር ትቶ ፤ ተቋሙ የደህንነት ስጋት እንደ አይፈጥር በመደበኛ የቁጥጥር ሥራ ወደ ማረጋገጥ ቢገባም።

በጀርመንም ተመሳሳይ አሠራር አለ።

ስለ እዚኽ፦ በተመሳሳይ የኢትዮጵያም መንግሥት ፤ ተመሳሳይ የወርቃማ አክሲዮን አሠራር አሰተዋውቆ ፦ ድርጅቱ በእሚሸጥበት ግዜ ለማን እንደ እሚሸጥ ፣ የዴታ ባለቤትነት ጉዳይ ላይ የሉዓላዊነት

ነገርን ማስገባት ፣ ብሔራዊ አስቸኳይ ግዜ ሲኖር ኔትዎርኩን በተለያየ መንገድ አክሰስ የማድረግ መብቶችል ለራሱ ሊሰጥ ይችላል።

ልክ እንደ ኔትዎርክ ተደራሽነቱ እና ለትርፍ መሥራት ፤ ብሔራዊ ደህንነት እና ገበያ ኹለት የእማይታረቁ ነገሮች አይደሉም።

አብረው ተቻችለው የእሚኖሩበት **የሕግ ማዕቀፍ** ብቻ ነው የእሚያስፈልጋቸው።

4.3 የኢትዮጵያ የካፒታል ማርኬት እንደ እዚኽ ዓይነት ሰፊ ፕሮጀክትን ፋይናንስ ሊያደርግ አይችልም

እስከ አኹን ከዓየናቸው ኹለት ሙግቶች ደካማው እና ቶሎ እሚሸነፈው ሙግት ይኽ ይመስላል። እርግጥ ነው የኢትዮጵያ የካፒታል ማርኬት ብዙ ገንዘብ እሚንቀሳቀስበት አይደለም። እንደ እዚኹም በረጅም ዘመን የእሚከፈል ብድርም ከእዚኽ ገበያ ማግኘትም አስቸጋሪ ነው።

ሆኖም ቴሌ አክሲዮን ልሸጥ ብሎ ሲወጣ ገበያው ያሳየው ፍላጎት ይኽን የተለመደ አመለካከት ጥያቄ ውስጥ የእሚያስገባ ነው። ቴሌ አንድ አክሲዮን በ300 ብር ልሸጥ ነው ሲል ፤ 47,377 ሰዎች አመልክተዋል።

በአንጻራዊነት ዝቅተኛ ገቢ አላት በእምትባል እና የገንዘብ ገበያው በደንብ አልዳበረም በእምትባለው ኢትዮጵያ ውስጥ 10.69 ሚልዮን ሼሮች እገዛለኹ የእሚላቸው ሰዎች አግኝተዋል።

ይኽ የቴሌኮም ኢንቨስትመንቶችን ፋይናንስ ማድረግ የእማይችል ገበያ ባሕሪ አይደለም ይልቁንም ዕድል የተነፈገ ገበያ ባሕሪ ነው።

ሳፋሪኮም የኢትዮጵያን ገበያ ለመቀላቀል ፤ የፈቃድ ብቻ የከፈለው 850 ሚልዮን ዶላር ፤ ከዓለም ዓቀፍ የገንዘብ ገበያ የተገኘ ነበር። ምክንያቱም ፦ ሳፋሪኮም ኢንቨስተሮቹ ጠንቃቃ ማኔጅመንት አለው ብለው ስለ አመኑበት።

ይኽን ዓይነት ገንዘብ ግን ቴሌ ከዓለም ዓቀፍ ኢንቨስተሮች ላያገኝ ይችላል ፤ ምክንያቱም ዓለም ዓቀፍ ኢንቨስተሮች ፤ በሳፋሪኮም ውጤታማነት እንደ እሚተማመኑት በቴሌ ውጤታማነት ስለ እማይተማመኑ።

የነገሩ ዋና ይኽ ነው ፤ ቴሌ እሚመራበትን ፍልስፍና ከተቀየረ ፤ ካፒታል በቀላሉ ይፈስለታል። ስለ እዚኽ ፦ የካፒታል ችግር ፤ ቴሌን በመንግሥት ሥር እንዲቆይ ግድ ይላል የእሚለው ሙግት ብዙም የተማረ ሙግት አይደለም።

በእርግጥ የማክሮ ኢኮኖሚው አስተማማኝነት ፤ ማለትም ፦ በሐገሪቱ የፖሊሲ ኹኔታ ላይም ይደገፋል።

4.4 የሲንጋፖር እና የኤምሬት አየር መንገድ በልማታዊ መንገድ ስኬታማ ሆነዋል

ይኸ አራተኛው ልማታዊያኖች የመስመራቸውን ትክክለኛነት ለማስረገጥ የእሚጠቀሙበት ሙግት ነው።

የሲንጋፖርን አየር መንገድ ብንወስደው ፤ ቴማሴክ ሆልዲንግስ (Temasek Holdings) በተባለው የሲንጋፖር መንግሥት ንብረት በአብዛኛ በባለቤትነት የተያዘ እና በዓለም ላይ ካሉት በጣም ትርፋማ እና ስኬታማ አየር መንገዶች አንዱ ነው።

ኢምሬትስ ደግሞ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የእሚተዳደር እና አኹን በዓለም ላይ በጣም ስኬታማ ሆኑ ከእሚባሉ አየር መንገዶች አንዱ ነው።

ኹለቱም የመንግሥት ንብረት መሆን ከተዋጣለት የዓለማችን ስኬታማ የንግድ ተቋምነት ያልገታቸው ናቸው።

ሆኖም ፤ የሲንጋፖር እና የኢምሬት አየር መንገዶችን በተለየ መንገድ ውጤታማ ያደረጋቸው በመንግሥት ባለቤትነት መያዛቸው ሳይሆን ፤ ይልቁንም የእሚተዳደሩበት መንገድ አስተዳደራዊ ጥራትን የእሚያረጋግጥ ፣ አመራሩ ከፖለቲካ ጣልቃገብነት እና ሹመት የጸዳ መሆኑ እና ለገበያ መርኽ የመገዛት ዲስፕሊን ያለው መሆኑ ነው።

ለምሳሌ ፦ የሲንጋፖሩ አየር መንገድ በጣም በበሰለ እና ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰ የገንዘብ ተቋማት አሠራር በመጠቀም ፤ የነዳጅ ዋጋ መጋሸብ እና የሲንጋፖር ዶላር ምንዛሪ መዳከም ለችግር እንደ አያጋልጠው ፤ የቀብድ አሠራርን (hedging) ይጠቀማል።

በቀጥይነት ወጪው ከዓለም ዓቀፍ ሌሎች ተመሳሳይ ተቋማት አንጻር እንዴት እንደ እሚወዳደር በእየግዜው ምዘና ያደርጋል።

ክዋና አስፈጻሚው ጀምሮ ያሉት የአየር መንገዱ ማኔጅመንቶች ባላቸው የፖለቲካ ታማኝነት እና ለፖለቲካዊ ፋይዳ ተብለው ሳይሆን ፤ ከመንግሥት ተፅዕኖ ነጻ በሆነ መንገድ ፤ የአየር መንገዱን ትርፋማነት እና ምርታማነት ለማረጋገጥ እንዲሠሩ ተብለው የእሚሾሙ ናቸው።

የኢትዮጵያ ቴሌ ግን ይኽን ዓይነት ገለልተኝነት የለውም ፤ እንዲያውም አንዱ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ዋና ማጠንጠኛ ፤ እንደ ቴሌ በአሉ የልማት በእሚባሉ የመንግሥት ድርጅቶች ውስጥ ማን በመሪነት ይሠራል የእሚለውን ለመቆጣጠር ይመስላል።

ከእዚኽ የተነሳ የሲንጋፖር አየር መንገድ ቢሆን ኖሮ እና እንደ ቴሌ የአገልግሎት ክፍያውን በሙሉ በውጭ ምንዛሪ ሳይሆን በሲንጋፖር ዶላር የእሚቀበል ቢሆን ኖሮ ፤ የ1.5 ቢልዮን የአሜርካ ዶላር ብድር

አይበደርም ነበር። ማኔጅመንቱ ይኽን ቢያስብ ፤ የሒሳብ ክፍሉ ፤ ይኽ ትክክል አይደለም ብሎ አልቀበልም ይለው ነበር።

እንደ እዚያውም ኢምሬትስ ፤ የተቋቋመው እና የእሚሠራው ፤ ጠቅላላው የሕግ እና የቁጥጥር ስረዓቱ በዋናነት የገበያ ተወዳዳሪነት ለማስቻል እንጂ ፖለቲካዊ ቁጥጥርን ለማረጋገጥ ባልሆነበት ዱባይ ውስጥ ነው። የማኔጅመንት ባሕሉ ዓለም ዓቀፋዊ እና ምርታማነትን በማሳደግ ላይ ያተኮረ ነው።

ተጠያቂነቱም ፤ ከፍተኛ የገንዘብ ኃብት ላለው እና የላቀ አየር መንገድ ለመሆን ፤ ከመንግሥት አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት ነጻ መሆን እንደ አለበት **ለእሚረዳ** መንግሥት ነው።

ስለ እዚኽ፦ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሲንጋፖር እና ከኢምሬት አየር መንገዶች መማር ያለበት ፤ የመንግሥት ባለቤትነት ያዋጣል ወይንም ይሠራል የእሚል ቢህል አይደለም።

ይልቁንም ፦ የመንግሥት ባለቤትነት ፦ በልዩ ኹኔታ ከፍተኛ አስተዳደራዊ ጥራት ሲኖረው እና ይኽም አስተዳደር (ማኔጅመንት) ከመንግሥት አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት ነጻ እና ገለልተኛ ሲሆን ሊሠራ ይችላል የእሚለውን ነው መማር ያለበት።

የኢትዮጵያ መንግሥት ግን የእዚኽ ዓይነት የአስተሳሰብ ብስለት ላይ ስለ አልደረሰ ፤ መሰል ስኬታማ የልማት ድርጅቶችን ፤ እንደ ማሳያ አድርጎ ሊጠቅስ አይገባም።

5 ምክረ ኃሳብ — ከተልዕኮ ወደ ገበያ ሽግግር

በቴሌ ላይ ይኽን ኹሉ ትችት አቅርበን ፤ የማሻሻያ ምክረ ኃሳብ ካላከልንበት ፤ ትችቱ ወደ መፍትኼ እሚያመራ አይሆንም።

የእዚኽ ጽሑፍ ዓላማም ፤ አኹን ቴሌ የእሚመራበት መንገድ አዋጭነት ብሎም ዘላቂነት የለውም ብቻ ሳይሆን ፤ የተሻለ አማራጭ አለ ፤ አማራጩም በደንብ የእሚታወቅ እና ለውጤታማነቱም ማስረጃ የሆነ ብዙ ተሞክሮዎች ያሉት ነው ብሎ ማሳየት ነው።

በመሆኑም ከእዚኽ በመቀጠል ፤ በማስረጃ የተደገፉ እና ከኢትዮጵያ ጋር ተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ ባሉ ሐገሮች ተሞክረው ውጤታማነታቸው ሐገራቱን ከአክሳሪ የልማታዊያን አካኼድ በማውጣት ያስመሰከሩ ታሪኮች ላይ የተደገፉ ፤ ምክረ ኃሳቦችን በዝርዝር ዕናያለን።

5.1 አንድ : መንግሥት በቴሌ ላይ ያለውን ባለቤትነት በ50% ይቀንስ

መንግሥት የቴሌን 50% ለገበያ አውጥቶ መሸጥ አለበት።

የመንግሥት እና የግሉ ዘርፍ ድርሻ 50-50 ሲሆን ፦ የዋጋ ትመና ፣ የብድር አስተዳደር ፣ የትርፍ ክፍፍል ፣ ወዘተ የመሰሉ ስትራቴጂክ ውሳኔዎች ፤ ከመንግሥት ወይንም ከግሉ ዘርፍ አንዱ በፈለገው መንገድ ሳይሆን ፤ ይልቁንም ሲስማሙ ብቻ ይሆናል።

በግሉ መስክ ተመርጦ የእሚመጣ የቦርድ አባል ፦ ምንም የደህንነት ዋስትና ሳይገባለት የ1.5 ቢልዮን ዶላር ብድር እንዲወሰድ አይፈቅድም ፣ ያወጣውን ውጪ የእማይሸፍን የዋጋ ትመና እንዲወጣ አይፈቅድም ፣ ምንም ማብራሪያ የሌላቸው ከተለያየ ምንጭ መጡ የእሚባሉ የ15 ቢልዮን ብር ገቢ እሺ ብሎ አይቀበልም ፣ ወዘተ።

ልክ ተጠያቂነቱ በገበያ የእሚታይ እና የእሚመዘን ቦርድ አባል ግማሽ የመወሰን አቅም ሲኖረው ፤ ያን ግዜ ፤ የቴሌ ማኔጅመንት ትንሳኤ ያገኛል።

በግዜ ኺደትም መንግሥት ቀስ እያለ ድርሻውን እየቀነሰ ፤ ወደ 35% አከባቢ የእሚያደርስ መሆን አለበት። በሌላ አነጋገር ግማሽ ድርሻው ጣራ ነው መሆን ያለበት ፤ ከግዜ ወደ ግዜ ዝቅ የእሚደረግ እና በፍጹም የእሚጨምር መሆን የሌለበት።

ለምሳሌ ፡- የጀርመን መንግሥት በደች ቴሌኮም ውስጥ የ31.9% ድርሻ አለው ፣ የፈረንሳይ መንግሥት ኦሬንጅ በእሚባለው የቴሌኮም ኩባንያው ውስጥ ወደ 13% መንግሥት በቀጥታ ፤ Bpifrance የእሚባለው የፈረንሳይ መንግሥት የኢንቨስትመንት ባንክ ደግሞ ወደ 9% በጠቅላላው 23% ገደማ ድርሻ አለው።

የኬንያ መንግሥት በሳፋሪኮም ውስጥ 35% ድርሻ አለው።

እነ እዚኽ ኹሉ መንግሥታት ፤ በቀጥታም በተዘዋዋሪም ፤ መቶ በመቶ የቴሌ ባለቤት ከሆነው መንግሥት በላይ ይጠቀማሉ።

5.2 ኹለት ፡ ገለልተኛ የሆነ የቴሌኮምንኬሽን መስክን የእሚቆጣጠር ባለስልጣን መሥሪያ ቤት ማቋቋም

አኹን ባለው ኹኔታ ኢትዮጵያ ውስጥ ገለልተኛ የሆነ እንደ ኬንያው የኮምኒኬሽን ባለስልጣን ወይንም እንደ ርዋንዳው የአገልግሎት[1] (መብራት ፣ ውኃ ፣ ስልክ ፣ ወዘተ) ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ዓይነት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን መሥሪያቤት ያለ አይመስልም።

ቁጥጥር ከተደረገም ቁጥጥር አድራጊው ተመልሶ ለእዚያው ቴሌን በባለቤትነት ለእሚያስተዳድረው የፖለቲካ ስልጣን ሪፖርት በእሚያደርግ ተቆጣጣሪ በመሆኑ ቁጥጥሩ ውጤታማ አይሆንም።

ተቆጣጣሪ አካል ግን ፤ ከአስፈጻሚው መንግሥት የስልጣን ተፅዕኖ ነጻ ሲሆን እና በጀቱ በቀጥታ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲወሰን (ወደ ፊት ገለልተኛ የሆነ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይኖራል በእሚል) ፤ ከፖለቲካ ተፅዕኖ በጸዳ መልኩ ውድድርን አረጋግጦ ለደንበኞች እና ለተገልጋዮች ከለላ መሆን ይችላል።

እንዲኽ ዓይነት ነጻ እና ገለልተኛ ተቆጣጣሪ ከሌለ ፤ ገበያው ቢከፈት እንኳን ፤ ነጻ እና ፍትኃዊ ውድድር ማረጋገጥ አብሮም የደንበኞችን ጥቅም ማስከበር ይከብዳል።

ለምሳሌ ፡- አኹን በቴሌ እና በሳፋሪኮም መካከል ፍትኃዊ ውድድር አለ ማለት አይቻልም።

በተመሳሳይም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና በሌሎች የግል ባንኮች መካከል ፍትኃዊ ውድድር አለ ማለት አይቻልም።

[1] ዩቲሊቲ (Utility) ለእሚባለው እና መብራት ፣ ውኃ፣ ስልክ ፣ ወዘተ ለእሚወክለው የእንግሊዘኛ ቃል ጥሩ የአማርኛ ቃል ስለሌለ ለምን ምጻረ ቃል አንጠቀምም ፡- ውመስ ፣ ስመው ፣ መውስ ፣ ወዘተ ዓይነት።

5.3 ሶሥት: ኹሉም በኢትዮጵያ ገበያ ለመሥራት ፈቃድ የእሚያገኙ የቴሌኮም አገልግሎት አቅራቢዎች መላ ሐገሪቱን በኔትዎርክ ሽፋን ለማዳረስ ስምምነት መፈረም አለባቸው

ለኢትዮጵያን ገጠራማ አከባቢዎች የኔትዎርክ ሽፋን ማዳረስ የልማታዊ መንግሥት ተልዕኮ ሳይሆን መሆን ያለበት የተቆጣጣሪው አካል ፈቃድ ሲሰጥ ኩባንያዎችን ግዴታ የእሚያስገባቸው ነው መሆን ያለበት።

እያንዳንዱ በኢትዮጵያ ገበያ ለመሥራት ፈቃድ የእሚያገኝ የቴሌኮም ኩባንያ ፤ ከገቢው የተወሰነ ያኽሉን ፤ ኔትዎርክ ለማስፋፋት እንዲጠቀምበት መፈረም አለበት። ይኽንንም ተቋጣጣሪ አካሉ ፤ ፈንዱን የመቆጣጠር እና ለታሰበው ዓላማ መዋሉን የማረጋገጥ ሥራ መሥራት አለበት።

የእዚኽ ጥቅሙም ፤ መንግሥት የጀብደኝነት ክስረት ውስጥ ሳያስገባ ፣ የውጭ ምንዛሪ ብድር ሳይፈጥር ብሎም ሌሎች ስውር ዋጋዎች ሳያስከፍል ፤ አትራፊው አከባቢ ደካማውን አከባቢ እንዲደጉም በማድረግ (cross-subsidy) ፤ የሐገሪቱን የኔትዎርክ ሽፋን ለማሳደግ ማስቻል ነው።

የሩዋንዳ ፣ የኬንያ እና የጋና ልምድ ይኽ አሠራር በአፍሪካ ውስጥ ውጤታማ ሊሆን እንደ እሚችል ማሳያ ነው።

5.4 አራት: የኢትዮጵያ የቴሌኮም ገበያ ለኹሉም ተወዳዳሪዎች ክፍት መሆን አለበት

በሐገራችን የቴሌኮም መስኩ ለውድድር ተከፍቶ ፤ ከእዚኽ በኋላ ወደ ገበያው መቀላቀል የእሚፈልጉ ኩባንያዎች ፤ በገለልተኛ ተቆጣጣሪ አካል ተቆጣጣሪነት የእሚረጋገጥ ፦ በሕግ መጠኑ ለኹሉም በእኩልነት የእሚወሰን እና የእሚታወቅ በገጠር ኢንቨስት የማድረግ ግዴታ ፣ የአገልግሎት ጥራት ግዴታ ፣ ወዘተ ውል እየፈረሙ ፤ ሌላ አላስፈላጊ የሆነ ልዩ የአገልግሎት ፈቃድ ክፍያ ሳይከፍሉ በወድድር ፈቃድ እንዲያገኙ መሆን መቻል አለበት።

5.5 አምስት: ቴሌ ከእዚኽ በኋላ በእሚያወጣቸው ዓመታዊ ሪፖርቶቹ የበለጠ ግልጸኝነት ሊኖራቸው ይገባል

አኹን ቴሌም ሆኑ ሌሎቹ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ፤ በዓለም ላይ ተቀባይነት ያለውን የIFRS መርኽ ተከትለው ዓመታዊ ሪፖርት ስለ እሚያዘጋጁ ፤ ዓመታዊ ሪፖርታቸው ብዙ ጠንካራ ግን አለው።

ሆኖም በባለቤትነት የእሚያዙት እና ኦዲት የእሚደረጉት ዞሮ ዞሮ በአንዱ የኢትዮጵያ መንግሥት ሥር ባለ የኦዲት ተቋም በመሆኑ ፤ ሆን ተብለው የእሚድበሰበሱ የዓመታዊ ሪፖርት አቀራረቦች አሉ።

በእርግጥ ቴሌ የባለቤትነት ውቅሩ ከተቀየረ ፤ ኦዲት የእሚያደርገው ገለልተኛ ተቋም እንደ እሚሆን ጥርጥር የለውም ፤ ሆኖም በአንዳች ምክንያት ግን በእዚኹ የመንግሥት ባለቤትነት ከቆየ ፤ በገለልተኛ ከተቻለ ፤ እንደ KPMG ባሉ የዓለማችን አውራ የኦዲት ተቋማት ከእሚባሉት አራቱ አንዱ በሆነው ተቋም ኦዲት መደረግ አለበት።

ለምሳሌ አኹን ቴሌ የIFRS መርኽ ተከትሎ ዓመታዊ ሪፖርት ቢሠራም ፡-

- ከፍተኛ የኩባንያው የማኔጅመንት አባላት ምን ያኽል እንደ እሚከፈላቸው ፥
- የማኔጅመንት አባላቱ ምን ለማሳካት እንደ ተቀጠሩ ፥
- ከመንግሥት ወደ ቴሌ በስጦታ ፣ በድጎማ ፣ ወዘተ የተላለፉ ድጎማዎች በሙሉ ፥ ወዘተ

በግልጽ ሲያቀርብ አይታይም።

በእርግጥ የ2025 ሪፖርት ላይ በተወሰነ ደረጃ ተካተዋል ፤ ሆኖም ፡- ተካተዋል ለማለት የተካተቱ እንጂ የቴሌን ቁመና እና አፈጻጸም ሊያሳዩ በእሚችሉ መልኩ አይደለም ያሉት።

አንድ እንደ ቴሌ ያለ ፤ ከመንግሥት/ከሕዝብ የ83.7 ቢልዮን ብር መሬት በስጦታ የእሚቀበል ፣ 16, 353 ሠራተኞች በመንግሥት ሠራተኝነት የእሚቀጥር እና ተጠያቂነቱ ለገበያ ሳይሆን ለመንግሥት ወይንም ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሆነ ኩባንያ ፤ ግልጸኝነቱ በአንድ በገበያ ከእሚመራ ተቋም በፍጹም ማነስ የለበትም።

5.6 ስድስት : ቴሌ በአስቸኳይ ገንዘቡን የሰበሰበበትን አክሲዮን ይደልድል (allotment immediately)

ይኽ በእርግጥ የመዋቅራዊ ለውጥ ምክረ ኃሳብ አይደለም ፤ አንድ ህሊና ያለው ሕዝብ ሊያከብረው የእሚገባው ግዴታ ነው። 47,377 የኢትዮጵያ ዜጎች ከሐገራቸው የቴሌኮም ኩባንያ አክሲዮን ለመግዛት ገንዘብ ክፈለው እስከ አኹን ምንም አላገኙም።

ገንዘቡ ተሰብስቧል ፤ የባለቤትነት ማረጋገጫ ግን አልተሰጠም።

ከቴሌ ኃብት አንጻር 3.21 ቢልዮን ብር ትልቅ ገንዘብ ስለ ሆነ አይደለም ፤ ይልቁንም መንግሥት ይኽን ማድረጉ ፤ ከእዚኽ በኋላ ለእሚደረጉት ማሻሻያዎች ያለውን ቁርጠኝነት በማሳየት ፤ ተዓማኒነቱን ከፍ ስለ እሚያደርገው ነው።

ዜጎች የባለቤትነት ማረጋገጫ ያልተቀበሉበትን አክሲዮን መሸጥ ፤ ለውጥ ወይንም ሪፎርም አይደለም ፤ ምን አልባት ከአንድ የመንግሥት ተቋም የእማይጠበቅ የገንዘብ ድጎማ የማሰባሰብ ሊሆን ይችላል።